እንደጦር የሚወጋ ጥያቄ

«ተመደኛስህን?» (ዮሐ. 21፣17)

በዚህ እንደጦር ለሚወጋ ጥያቄ ጴጥሮስ የሰጠው መልስ ከጥቂት ቀኖች በፊት አሳይቶት ከነበረው ድፍረት በጣም የተለየ ነው። ከጥቂት ቀኖች በፊት «ከአንተ ጋር መሞት እንኳ የሚያስፈልገኝ ቢሆን ከቶ አልክድህም» ብሎ ነበር (ማቴ. 26፣35 በተጨማሪም ከቊጥር 33-34 ይመለከቷል)። ተፈጥሮአዊ ባሕርያችን ወይም እኔነታችን የተሰማውን ሁሉ በድፍረት የመናገር ባሕርይ አለው። ይሁን እንጂ በጥልቅ መንፈሳችን ውስጥ ያለው እውነተኛ ፍቅር የሚገለጸው ኢየሱስ ባቀረበው ዓይነት ጥያቄ ልባችን ሲወጋ ነው። ጴጥሮስ አየሱስን ይወደው የነበረው ማንም ቢሆን መልካሙን ሰው በሚወደድበት ዓይነት ሁኔታ ነበር። ይህ ግን ስሜታዊ እንጂ ጥልቅ ፍቅር አይደለም። ስሜታዊ ፍቅር ተፈጥሮአዊ እኔነትን ይነካል እንጂ የሰውን ጥልቅ መንፈስ ዘልቆ አይገባም። እውነተኛ ፍቅር «እኔ እንዲህ ነኝ» ብሎ በወሬ ራሱን አይገልጽም። ኢየሱስ «በሰው ፊት የሚመሰክርልኝ ሁሉ (በአንደበቱ ብቻ ሳይሆን በሚያደርገው ነገር ሁሉ ፍቅሩን የሚገልጽልኝ) የሰው ልጅ ደግሞ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ይመሰክርለታል» አለ (ሉቃ. 12፣8)።

ስለራሳችን ያለንን የተሳሳተ ግምት ፊት ለፊት በመጋፈጥ ጉዳቱን ካላረጋገጥን በሕይወታችን የእግዚአብሔር ቃል የሚፈለገውን ሥራ አልሠራም ማለት ነው። ከኃጢአት በባሰ ሁኔታ የእግዚአብሔር ቃል ልባችንን ይወጋል፣ ምክንያቱም ኃጢአት ስሜታችንን ያደነዝዛል። ይህ ኢየሱስ ያቀረበው ጥያቄ ግን ከምንም ነገር ይልቅ ሕመሙ እንዲሰማን ልባችንን ንቁ ያደርጋል። ጉዳቱ ለተፈጥሮአችን ብቻ ሳይሆን ለጥልቅ መንፈሳችንም ዘልቆ ይሰማል። «የእግዚአብሔር ቃል ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለ ነው፣ ነፍስንና መንፈስን እስኪለይ ድረስ ይወጋል» (ዕብ. 4፣12)። ምንም ዓይነት ሽፍጥ ወይም ማስመሰል እስከማይኖር ድረስ ልብን ይወጋል። ጌታ በቀጥታ ሲናገረን ልንቋቋመው በማንችለው ሁኔታ ሕመሙ ጽኑ ነው፣ ይሁን እንጂ ሕመሙ የሚሰማው ከእርሱ ፈቃድ ጋር የማይስማማውን እኛነታችንን ነው። የጌታ ቃል ልባቸውን ሲወጋው የእግዚአብሔር ልጆች ከማን እንደሆነ ያውቃሉ፤ ያ ጊዜ እውነትን ለእኛ የሚገልጽበት ጊዜ ነው።

እስኪቆጠቁጥህ ድረስ ጌታ ነክቶሃልን?

«ሦስተኛ ጊዜ፣ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣ ትወደኛለህን ስለው» (ዮሐ. 21፣17)

ፕልቅ እኛነታችንን ወይም ደግሞ በጣም የሚያምና የሚቆጠቁጥ የሕይወት ገጽታችንን በሚዳሰስ መልኩ ጌታ ነክቶን ያውቃልን? ሰይጣንም ሆነ ኃጢአት ወይም ሰብዓዊ ስሜት ይህን የሕይወት ገጽታችንን መንካት አይችሉም። ወደ ጥልቅ እኛነታችንና ይበልጥ ወደሚያመን የሕይወታችን ክፍል መዝለቅ የሚችል የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። «ሦስተኛ ጊዜ ትወደኛለህን ስላለው ጴጥሮስ አዘነ» ይሁን እንጂ ከምንጊዜውም ይልቅ ሕይወቱ ለክርስቶስ የተሰጠ እንደሆነ ጴጥሮስ የተረዳው ያኔ ነበር። ይህ ተደጋጋሚ ጥያቄ ምን ማለት እንደሆነ ማስተዋል የጀመረውም ያኔ ነበር። በዚያ ጊዜ በጴጥሮስ አእምሮ ውስጥ ምንም ጥርጥር አልነበረም። ከእንግዲህ ወዲህ እንዳለፈው ጊዜ አይሳሳትም፣ እንዳለፈው ጊዜ አሁን ስሜታዊ አይደለም፤ ወኔ በተሞላበት ሁኔታ መልስ መስጠትም አይፈልግም። ጌታን የመውደዱ ልክ ምን ያህል እንደሆነ ለመረዳት የሚያስችለው ልዩ መገለጥን አግኝቶአል። ስለዚህም በመገረም «ጌታ ሆይ፣ አንተ ሁሉን ታውቃለህ» አለው። ለጌታ ያለው ፍቅር ምን ያህል እንደሆነ አሁን ገብቶታል። ስለዚህም «ይህንና ያንን አድርጌአለሁ፤ ይህ ራሱ እንደምወድህ ማስረጃ ሊሆን ይችላል» ማለት አልፈለገም። አሁን አቅሙን አውቆአል፣ አሁን ልኩን አውቆአል፤ ለጌታ ያለው ፍቅር ምን ያህል እንደሆነም ማወቅ ጀምሮአል ከእንግዲህ ወዲህ ዓይኖቹን በኢየሱስ ላይ አድርጎአል፤ በላይ በሰማይ በታችም በምድር ምንንም አያይም። ይሁን እንጂ ይህን የተረዳው የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጥያቄ ልቡን ከወጋውና ካሳመመው በኋላ ነበር። ምንጊዜም ቢሆን ጌታ የሚያቀርበው ጥያቄ እውነተኛ ማንነታችንን ያሳየናል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለጴጥሮስ ያሳየው ትዕግሥትና የተጠ ቀመበት ጥበብ ምንኛ ቀጥተኛና ጥልቅ ነው! ጌታ ጥያቄ የሚያቀርብልን በትክክለኛው ጊዜ ነው። አልፎ አልፎ፣ ምናልባትም በሕይወት ዘመናችን አንድ ጊዜ እንዲህ ያለ ልብን የሚወጋና በፍጹም የማንሸሸው ጥያቄ ያቀርብልናል። በዚያን ጊዜ አንደበታችን መግለጽ ከሚችለው በላይ እርሱን እንደምንወድ ከምንጊዜውም ይልቅ ይታወቀናል።

እርሱ የሰጠን አደራ

«በጎቼን ስሰማራ» (ዮሐ. 21፣17)

ይህ ፍቅር በተግባር ሲገልጽ ነው። እግዚአብሔር ፍቅርን ከጊዜ በኋላ አልተማረውም፣ ፍቅር ባሕርዩ ነው። በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የክርስቶስን ሕይወት ስንቀበል ፍቅሩ በሕይወታችን ይታይ ዘንድ ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት እንዲኖረን ያደርጋል። የመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን መኖር ዓላማ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔርጋር አንድ በሆነበት ሁኔታ እኛንም ወደዚያ ኅብረት ማምጣት ነው። ለመሆኑ፣ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው አንድነት ምን ዓይነት ነበር? ሕይወቱን ለእኛ ለመስጠት ሲልከው ታዛዥ እስከ መሆን ድረስ ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት ነበረው። እኛንም «አባቴ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ» ብሎናል (ዮሐ. 20፣21)።

ጌታ ያቀረበለት ጥያቄ ልቡን ከወጋው ወዲህ ጴጥሮስ ጌታን እንደሚወድደው ተገንዝቦአል። ቀጥሎ ደግሞ ጌታ ጴጥሮስን ያዘዘው «ሕይወትህን ስጥ፣ ምን ያህል እንደምትወደኝ በቃልህ መመስከር የለብህም፣ ስላገኘሽው አስደናቂ መገለጥ መናገርህን አቁም፣ በጎቼን አሰማራ» በማለት ነበር። ኢየሱስ የተለያየ ጠባይ ያላቸው በጎች አሉት። አንዳንዶቹ ቆሽሸዋል፣ አንዳንዶቹ ድንጉጥና በቀላሉ የሚበረግጉ ናቸው፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ከእረኛው ተለይተው እየባዘኑ ነው። ይሁን እንጂ ለእነዚህም ቢሆን የእግዚአብሔር ፍቅር ሰፊ ነው። እኔም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የእርሱ ፍቅር ወደ ልቤ ከፈሰሰ እነዚያን በጎች ባሉበት ሁኔታ እወድዳቸዋለሁ። የእግዚአብሔር ፍቅር እኔ የማቀርበውን ትችትና ንቀት ግምት ውስጥ አያስገባም። በእውነት ጌታን የምወድድ ከሆነ በራሴ ስሜት መመራት የለብኝም፣ በጎቼን መመገብ አለብኝ። ለዚህ ኢየሱስ ለሰጠን ትእዛዝ ምንጊዜም ቢሆን ባለአደራዎች ነን። አንዳንድ ጊዜ የእኛን ተፈጥሮአዊ ስሜት ማለትም መራራትና መቆርቆራችንን እንደ እግዚአብሔር ፍቅር የመመልከት ዝንባሌ አለን። ከእንዲህ ዓይነት ስሕተት እንጠንቀቅ። እንዲህ ዓይነት ዝንባሌ ስለእግዚአብሔር ፍቅር የተሳሳተ አመለካከት እንዲኖረን ያደርጋል።

እኔስ እንዲህ ማለት እችላለሁን

«ከጌታ የተቀበልሁትን ስገልግሉት ስፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደከንቱ ነገር እቁጥራለሁ» (የሐዋ. 20፣24)

ያለምንም ራዕይ ወይም ጥሪ እግዚአብሔርን ማገልገል ቀላል ነው፤ ምክንያቱም የምናገለግለው በዚያ መልክ ከሆነ የእርሱን መስፈርት የማሟላት ግዴታ አይኖርብንም። በዚያን ጊዜ በክርስቲያናዊ ፍቅር ሽፋን የሚመራን የራሳችን ስሜትና ተፈጥሮአዊ ግንዛቤ ይሆናል። የእግዚአብሔርን ጥሪ እሺ ብለህ ባትቀበል በዓለም መስፈርት አንጻር ባለጸጋ መሆን! ትችላለህ፤ ነገሮችም ይሳኩልህ ይሆናል፤ የምትዝናናበት በቂ ጊዜ ይኖርህም ይሆናል። ከጌታ መመሪያን ተቀብለህ ከሆነ ከእርሱ የተቀበልኸው ትእዛዝ ትዝ ባለህ ቍጥር ፈቃዱን ለማድረግ ልብህ ይነሣሣል። በተፈጥሮአዊ ግንዛቤህና ሥጋዊ ስሜትህ ግን በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ እርሱን ማገልገል አትችልም።

በሕይወቴ ውድ ወይም ክቡር የሆነብኝ ነገር ምንድን‌ነው? ሙሉ በሙሉ ሕይወቴን ለኢየሱስ ክርስቶስ ያልሰጠሁ ከሆነ ምናልባት እግዚአብሔርን ለማገልገል የማውለው ጊዜ ወይም የምጠቀምበት ዘዴ ውድ ወይም ክቡር ነገር ሆኖብኝ ይሆናል። ምናልባትም ውድ ወይም ክቡር የሆነብኝ የገዛ ራሴ ሕይወት ሊሆን ይችላል። ጳውሎስ ግን የተቀበለውን አገልግሎት ለመፈጸም ነበር ውድ ወይም ክቡር ሕይወቱን ያዋለው። ኃይልና ጉልበቱን ለሌላ ለምንም ነገር ማባከን አልፈለገም። እላይ ከተመለከትነው ጥቅስ መረዳት እንደሚቻለው ስለራሱ ሕይወት እንዲያስብ በቀረበለት አማራጭ ጳውሎስ ጨዋነት ባለው ሁኔታ የተረበሸ ይመስላል። የተቀበለውን አገልግሎት ከመፈጸም በቀር ለሌላ ነገር ደንታ አልነበረውም። አንዳንድ ጊዜ ለአገልግሎት የምናቀርበው ምክንያት ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ ከተሰጠ ሕይወት በተቃራኒ ይሆናል። «እኔኮ ለአገልግሎት በጣም የማስፈልግ ሰው ነኝ። በሕይወት ብኖር ገና ብዙ የምሠራው ይኖራል» በማለት መከራከሪያ እናቀርባለን። እንደዚህ ከሆነ ደግሞ የት መሄድ እንዳለብንና ምን ማድረግ እንዳለብን የሚወስንልን የራሳችን አእምሮ እንጂ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለም ማለት ነው። ምንጊዜም ቢሆን የእኛን አስፈላጊነት ግምት ውስጥ ማስገባት የለብንም፤ ምክንያቱም እኛ የራሳችን አይደለንም። «የራሳችሁ አይደላችሁም» (1ቆሮ. 6፣ 19)። የእርሱ ነን።

በእርግጥ እርሱ የሕይወቴ ጌታ ነውን?

«ፈጣዩንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን ለገልገሉት በደስታ ስፈጽም ዘንድ...»

(የሐዋ. 20፣24)

ደስታ የሚኖረኝ እኔ የመረጥሁትን ነገር በማከናወኔ ሳይሆን የተፈጠርሁበትን ከዚያም በላይ ደግሞ ዳግም የተወለድሁበትን ልዩ ዓላማ ፈጽሜ ስገኝ ነው። ጌታ ደስ ይሰኝ የነበረው የአባቱን ፈቃድ በማድረጉ ነበር። እርሱ ደግሞ እኛን «አባቴ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ» ብሎናል (ዮሐ. 20፣21)። ከጌታ የተቀበልኸው አገልግሎት ይኖርህ ይሆን? እንደዚያ ከሆነ ለተቀበልኸው አገልግሎት ታማኝ መሆን ይኖርብሃል። የሕይወትህ ዓላማና ግብ አገልግሎትህን መፈጸም ይሁን። ኢየሱስ የሰጠህን አገልግሎት ፈጽመህ በመገኘትህ «አንተ ታማኝ ባሪያ መልካም አድርገሃል» ሲልህ የሚሰማህን ደስታ አስብ (ማቴ. 25፣21)። እያንዳንዳችን ዓላማና ግብ ሊኖረን ይገባል። በመንፈሳዊ መልኩ ይህን ዓላማና ግብ የምናገኘው ደግሞ ከጌታ የተቀበልነው አገልግሎት ሲኖረን ነው። ይህ እንዲሆን ከኢየሱስ ጋር የጠበቀ ጎብረትና ግንኙነት ይኑረን። ኢየሱስ ከአዳኛችንም በላይ መሆን አለበት። በሐዋርያት ሥራ 9፣16 የተጻፈው «ስለስሜ ስንት መከራ ሊቀበል እንዲያስፈልገው እኔ አመለክተዋለሁ» የሚለው ቃል ለእኛም ጭምር እንደተነገረ ማመን አለብን።

«ትወደኛለህን?» ካለ በኋላ «በጎቼን አሰማራ» ብሎአል (ዮሐ. 21፣17)። ጌታ ይህን ሲል እርሱ የሰጠንን አገልግሎት በታማኝነት እንድንፈጽም እንጂ መልካም መስሎ በታየን ሁኔታ እንድናገለግለው ምርጫ እያቀረበልን አይደለም። ይህም ሊሆን የሚችለው ከእግዚአብሔር ጋር የሰመረ ጎብረትና ግንኙነት ሲኖረን ብቻ ነው። ከጌታ ጥሪ ተቀብለህ ከሆነ ጥሪና ተግባር የተለያዩ ነገሮች እንደሆኑ ትረዳለህ። ተግባር ጥሪህን ሥራ ላይ ማዋልህን ያመለክታል። ጥሪ ደግሞ ከእርሱ ጋር ከነበረህ ጎብረት የተነሣ ለተሰጠህ አገልግሎት ታማኝ መሆንን ያመለክታል። እንዲህ ሲባል ግን የግድ አንተ ብቻ የምትፈጽማቸው የአገልግሎት ዓይነቶች ይኖሩሃል ማለት ሳይሆን ከጌታ ለተቀበልኸው ጥሪ ምን ጊዜም ንቁ መሆን አለብህ ማለት ነው። ይህም በየጊዜው የሚከፈቱ የአገልግሎት በሮችን አለመቀበል ሊሆን እንኳ ይችላል።

ቀጣዩን እርምጃ መወሰድ

«በብዙ ተዕግሥት፣ በመከራ፣ በችግር፣ በጭንቀት...» (2ቆሮ 6፣4 ስ.መ.ት.)

ከእግዚአብሔር የተቀበልነው ራዕይ በማይኖረን ጊዜ ጉትጉትና ናፍቆታችንን የሚያነሣሣ ነገር አይኖረንም፤ ልብ ብሎ የሚያስተውለንና አይዞአችሁ የሚለን ሰው ላይኖረንም ይችላል፤ በዚህ ጊዜ ሕይወት አሰልቺ ስለምትሆንብን ቀጣዩን እርምጃ ለመውሰድ ልዩ ጸጋ ያስፈልገናል። መጽሐፍ ቅዱሳችንን ለማንበብና ለማጥናት፣ ለጸሎትና ለቤተሰብ ሕይወታችን፣ ለእርሱ በታማኝነት ለመኖር ከምንጊዜውም የተለየ ጸጋ ያሻናል። በዚህ ወቅት የሚያስፈልገን ጸጋ ቃሉን ለመስበክ ከሚያስፈልገን ጸጋ እጅጉን የሚበልጥ ነው።

የሚያነሣሣን ራዕይ ላይኖር ሲቀር ስሜታችን ይቀዘቅዛል፣ አጽናኝና የሚያበረታታን ስለማይኖር፣ እንዲሁም በሥራችን ምንም መከናወን ስለማይታይ በቀላሉ ተስፋ እንቈርጣለን፤ ያኔ ፊት ለፊታችን የሚታየን አሰልቺ የዕለት ተዕለት ሥራ ብቻ ነው። ይሁን እንጂ ሥራው አሰልቺና አታካች ሲሆን፣ ማንም ባያየንና ባያበረታታንም በትዕግሥትንና በጽናት ተግባራችንን እንፈጽም። የኋላ ኋላ የእግዚአብሔርና የሕዝቡ ምስክር የሚሆነውም በዚህ ወቅት የምናሳየው ጽናትና ትዕግሥት ነው። በሁኔታዎች የማይሸነፍ ሕይወትን ለመኖር ብቸኛው መንገድ ዓይናችንን በእግዚአብሔር ላይ ማድረግ ነው። ስለሆነም መንፈሳዊ ዓይኖችህን ሞትን ድል አድርጉ የተነሣው ጌታ ላይ እንድታደርግ እንዲረዳህ እግዚአብሔርን ለምነው፤ ያኔ ሁኔታው ምንም አሰልቺና አታካች ቢሆንም በፍጹም ተስፋ አትቈርጥም። አንዳንድ ሥራዎችን በፍጹም ለክብሬ አይመጥኑም ከማለት ተጠበቅ፤ ይህማ በጣም ዝቅተኛ ነው በማለት ማንኛውንም ሥራ አትናቅ፤ ምንጊዜም ቢሆን በዮሐንስ 13፣1-17 የቀረበውን የጌታን ምሳሌነት አስታውስ።

ከመጠን ይልቅ የበዛ ደስታ ምንጭ

«በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከሰሸናፊዎች እንበልጣለን» (ሮሜ 8፣37)

እዚህ ላይ ጳውሎስ አንድን ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ፍቅር መነጠል የሚችሉ ስለሚመስሉ ነገሮች ይናገራል። ዋናው ቁም ነገር ግን በእግዚአብሔር ፍቅርና በእውነተኛ ክርስቲያን መካከል ምንም ነገር ጣልቃ መግባት አለመቻሉ ነው። በዚህ ምንባብ ጳውሎስ የዘረዘራቸው ነገሮች ነፍሳችን ከእግዚአብሔር ጋር ያላትን የጠበቀ ግንኙነት ለጊዜውም ቢሆን ማወክ ይችላሉ፣ ተፈጥሮአዊ ሕይወታችንንም ከእርሱ ይለያሉ። በመንፈሳዊ ደረጃ ግን አንዳቸውም ቢሆኑ በእግዚአብሔር ፍቅርና በነፍሳችን መካከል ጣልቃ ሊገቡ ወይም ሊለዩን አይችሉም። የክርስትና እምነት መሠረት በቀራንዮ መስቀል ላይ የተገለጸው ወሰን የለሽ የእግዚአብሔር ፍቅር ተአምር ነው። ይህ ፍቅር ለመልካም ሥራችን የምናገኘው ሽልማት አይደለም። ጳውሎስ «በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ለአሸናፊዎች እንበልጣለን» የሚለውም በዚህ ምክንያት ነው። ሊያሸንፉን ወይም ሊያጠፉን የመጡ በሚመስሉ ነገሮች ላይ ድል አድራጊዎች ነን።

በዋና የሚሻገርን ሰው የሚያስፈራው ማዕበል፣ በጀልባ ለሚቀዝፍ ሰው ግን ደስ ሊያሰኘው ይችላል። በማንኛውም ሁኔታዎች ውስጥ ስናልፍ ይህን እናስታውስ። ልናስወግዳቸው ወይም ልንታገላቸው የምንሞክረው ነገሮች ማለትም መከራ ችግርና ስደት የበለጠውን ደስታ እንድንለማመድ ምክንያት ሊሆኑልን ይችላሉ። «በዚህ ሁሉ በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።» እዚህ ላይ «በዚህ ሁሉ» ሲል በሕይወት በሚገጥሙን የተለያዩ ችግሮች ሁሉ ማለቱ ነው። ደስታችን በእነዚህ ነገሮች ውስጥ በማለፍ እንጂ ከእነዚህ ነገሮች በመሸሽ አይደለም። አንድ ክርስቲያን የጌታን ደስታ የሚለማመደው ሁሉም ነገር መልካም ስለሆነለት ሳይሆን፣ በመከራና በችግር ውስጥ ነው። ጳውሎስ «በመከራችን ሁሉ ደስታዬ ከመጠን ይልቅ ይበዛል» አለ (2ቆሮ. 7፣4)።

እውነተኛ ደስታ የሚገኘው በሚያልፉ በዚህ ዓለም ነገሮች ላይሆን ምንም ነገር በማይለውጠው በእግዚአብሔር ፍቅር ነው። በዚህ ሕይወት የሚገጥመን ውጣ ውረድ «በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ» (ሮሜ 8፣39)።

ሙሉ በሙሉ የተሰጠ ሕይወት

«ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ» (ገላ. 2፣20)

ከኢየሱስ ጋር አንድ መሆን ከተፈለገ አንድ ሰው ኃጢአትን መተው ብቻ ሳይሆን ለነገሮች ያለውን አመለካከትም ሙሉ በሙሉ ለእርሱ ለማስገዛት ፈቃደኛ መሆን አለበት። ከእግዚአብሔር መንፈስ ዳግም መወለድ ማለት አዲሱን ነገር ለመያዝ ቀድሞ የያዝነውን ነገር መተው ማለት ነው። በመጀመሪያ መተው ያለብን ነገር፣ መስለን ለመታየት የምናደርገውን ሙከራና ሽንገላ ነው። ጌታ እንድንሰጠው የሚፈልገው መልካም ነገራችንን፣ ታማኝነታችንና የራሳችንን ሙከራ ሳይሆን ኃጢአታችንን ነው። በኃጢአታችን ምትክ ደግሞ ከእርሱ ጽድቅን እንቀበላለን። ይሁን እንጂ አስቀድመን ስለራሳችን ያለንን የተሳሳተ አመለካከት መተው አለብን። የእግዚአብሔር ልብ ያርፍብን ዘንድ የበቃን አለመሆናችንን ማወቅ አለብን።

ያንን ካደረገን በኋላ ደግሞ ቀጥሎ አሳልፈን የምንሰጠውን ወይም ለእርሱ የምናስገዛውን ነገር የእግዚአብሔር መንፈስ ያመለክተናል። ከዚህ ሂደት ጎን ለጎን መብቴ ነው የምንለውንም ነገር መተው ይኖርብናል። ታዲያ የእኔ ነው የምንለውን ምኞታችንና ሌላው ነገራችንን በሙሉ ለእርሱ ለማስገዛት ፈቃደኞች ነን? ከኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ጋር ለመተባበር ዝግጁ ነን?

ሙሉ በሙሉ ራሳችንን ከመስጠታችን ወይም ከማስገዛታችን በፊት ከነበረን ነገር መቆራረጥ አለብን፤ ይህም ደግሞ ሊያምመን ይችላል። ሰዎች ጌታ እንደሚያያቸው ራሳቸውን ማየት ሲጀምሩ በጣም የሚያሳዝናቸውና ልባቸውን የሚያደማው ኢየሱስ ክርስቶስን ሊቃወም የኖረው የልባቸው ትዕቢት እንጂ ሊያደርጉት የነበረው ኃጢአት አይደለም። በጌታ ብርሃን ራሳቸውን ማየት ሲችሉ ምን ያህል በደለኛ እንደነበሩ ይታወቃቸውና በጣም ያፍራሉ፤ በጣም ይጸጸታሉ።

ራስህን ሙሉ በሙሉ የመስጠት ወይም ያለመስጠት ጥያቄ ሲገጥምህ ምንም እንኳ የራሱ ውጣ ውረድ ቢኖረውም ራስህንና ያለህን ነገር ሁሉ ለእርሱ ለማስገዛት ወስን፤ በዚያን ጊዜ እርሱ ከአንተ የሚጠብቀውን ሁሉ የምታደርግበትን ኃይል እግዚአብሔር ይሰጥሃል።

ከኢየሱስ ጋር መራመድ ወይስ ወደ ኋላ መመለስ?

«እናንተም ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁን?» (ዮሐ. 6፣67)

ሃጢአ ንኛ ልብን ዘልቆ የሚገባ ጥያቄ ነው ጌታ ይሚጠይቀው! ቀላል በሆነ ሁኔታ ቢሆንም ምን ጊዜም እርሱ ሲናገር ወደ ልባችን ዘልቆ ይገባል። ምንም እንኳ የኢየሱስ ማንነት የተረዳን ቢሆንም እርሱ «እናንተም ልትሄዱ ትወዳላችሁን?» በማለት ይጠይቀናል። እኛ ግን ችግርና መከራ እንደሚጠብቀን ብናውቅም፣ የምንከፍለው ዋጋ ቢኖርም፣ ከእርሱ ጋር መጓዝን እንምረጥ።

«ከዚህም የተነሣ ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ወደ ኋላ ተመለሱ ወደ ፊትም ከእርሱ ጋር አልሄዱም» (ዮሐ. 6፣66)። ከኢየሱስ ጋር መራመድ አልፈለጉም። ጥዞአቸው ወደ ኃጢአት ባይሆንም ከእርሱ ርቀው ሄዱ። ብዙዎች በአገልግሎት ወዲያ ወዲህ ይላሉ፣ ብዙ ይደክማሉ፣ ይሁን እንጂ በእውነት ስንመለከተው ከእርሱ ጋር አይራመዱም፣ ከእርሱ ጋር አይሄዱም። እግዚአብሔር ደግሞ ደጋግሞ ከእኛ የሚጠይቀው ነገር ቢኖር ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድነት እንዲኖረን ነው። ሕይወታችንን በመቀደስ እግዚአብሔር ለራሱ ከለየን በኋላ ከእርሱ ጋር ያለንን አንድነትና ኅብረት ለመጠበቅ በመንፈሳዊ ረገድ ራሳችንን ማስለመድ አለብን። እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ፈቃዱን ግልጽ ካደረገልህ ከእርሱ ጋር ያለህን ኅብረት ለመጠበቅ የምትጠቀምበት የራስህ መንገድ በፍጹም አስፈላጊ አይደለም። በኢየሱስ ላይ በመደገፍ መንፈሳዊ ሕይወትህን መምራት ብቻ ነው የሚጠበቅብህ። ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ሕይወት በራሱ መንገድ ነው መኖር ያለብህ፣ የእርሱ መንገድ ደግሞ ሙሉ በሙሉ የመስጠት መንገድ ነው። ወደ ፊት የሚጠብቀን ነገር ምን እንደሆነ እርግጠኛ ባንሆንም ከእርሱ ጋር መሄዳችንን እንቀጥል፣ ከእርሱ ጋር የመሄድ ሥነጢርም ይኸው ነው።

ጴጥሮስ ኢየሱስን የሚያውቀው ለዓለምና ለእርሱም ደኅንነትን መስጠት በመቻሉ ብቻ ነበር። ይሁን እንጂ ጌታ አብረነው እንድንሠራ ይፈልጋል።

ከቀኖጥር 70 እንደምንመለከተው ከእርሱ ጋር ለመሆን መመረጡን ፍቅር በተመላበት ሁኔታ ኢየሱስ ለጴጥሮስ ነግሮታል። «እናንተም ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁን?» ለሚለው ጥያቄ እያንዳንዳችን በግላችን መልስ መስጠት አለብን።

የመልእክቱ ምሳሌ መሆን

«ቃሉን ስበክ» (2ጢሞ. 4፣2)

ክርስቲያንነትን ያገኘነው የእግዚአብሔር የጽድቅ መሣሪያዎች እንድንሆን ብቻ ሳይሆን ለእርሱ ወንዶችና ሴቶች ልጆች አንድንሆንለት ነው። መንፈሳዊ መልእክተኞች እንጂ መንፈሳዊ ጉዳይ አስፈጻሚዎች አይደለንም። መልእክቱ የሕይወታችን ክፍል መሆን አለበት። የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ራሱ የእግዚአብሔር መልእክት ነው። «እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው» (ዮሐ. 6፣63)። የእርሱ ተከታዮች እንደ መሆናችን መጠን ሕይወታችን የምናስተላልፈውን መልእክት እውነተኛነት የሚያረጋግጥ መሆን አለበት። የአንድ ሰው ሕይወት የእግዚአብሔርን መልእክት እውነተኛነት ማንጸባረቅ የሚችለው ኃጢአተኝነቱን ሲረዳ፣ በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቅና ሙሉ በሙሉ ሕይወቱን ለእግዚአብሔር ዓላማ ሲሰጥ ነው።

ምስክርነት መስጠትና ቃሉን መስበክ በጣም የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ቃሉን የሚሰብክ ሰው ጥሪ የደረሰውና የእግዚአብሔርን እውነት ለማወጅ መላው ሕይወቱን የሰጠ ነው። ከጸንጠቆስጤ ቀን በኋላ በደቀ መዛሙርቱ ሕይወት እንደ ተጠቀመ ሁሉ እኛንም እግዚአብሔር ለሕይወታችን ከነበረን ምኞት አላቅቆ ለራሱ ዓላማ መፈጸሚያ ይጠ ቀምብናል። የጰንጠቆስጤ ልምምድ ዓላማ ለደቀ መዛሙርቱ አንድ አዲስ ትምህርት መስጠት አልነበረም፣ ዓላማው ሲሰብኩት የነበረውን እውነት በሕይወታቸው እንዲኖሩት ማድረግ ነው። «ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» (የሐዋ. 1፣8)። ቃሉን ስትሰብክ እግዚአብሔር እንዲጠ ቀምብህ ራስህን ስጠው። የእግዚአብሔር መልእክት ሌሎችን ነጻ ከማውጣቱ በፊት ነጻ የማውጣቱ ኃይሉ በግል ሕይወትህ እውን መሆን ይኖርበታል። ለስብከት የሚሆንህን መልእክት በጥንቃቄ ካዘጋጀህ በኋላ ለእርሱ ክብር ይሆን ዘንድ ቃልህ በእግዚአብሔር እሳት ይቀጣጠል።

ለሰማያዊው ራዕይ መታዘዝ

«ከሰማይ የታየኝን ራዕይ እንቢ ስላልሁም» (የሐዋ. 26፣19)

እግዚአብሔር የሰጠን ራዕይ ከጠፋብን ጎላፊነቱ የእኛ እንጂ የእግዚአብሔር አይሆንም። ራዕዩ የሚጠፋብን ከራሳችን መንፈሳዊ ሕይወት እድገት ማጣት ነው። ስለእግዚአብሔር የተረዳነውን ጉዳይ በየዕለቱ ሕይወታችን ተግባራዊ ካላደረግነው እርሱ የሰጠን ራዕይ አይፈጸምም። ከሰማይ ለተገለጠልን ራዕይ ታዛዥ የምንሆንበት ብቸኛው መንገድ ሁለንተናችንና ውድ የሆነብንን ነገር ለእርሱ ክብር በመስጠት ነው። ይህ ሲሆን የሚችለው ደግሞ ዘወትር የእግዚአብሔርን ራዕይ ስናስታውስ ብቻ ነው። መታዘዝ ስንል በግል የጸሎት ጊዜያችን ወይም ለአምልኮ የምንሰበሰብበትን ጊዜ ብቻ ሳይሆን የሕይወታችንን ጥቃቅን ጉዳዮችን እንኳ ሳይቀር የሚያካትት ነው።

«ቢዘገይም በእርግጥ ይመጣልና ታገሠው» (ዕን. 2፣3)። በጥረታችን ራዕዩ እንዲፈጸም ማድረግ አንችልም፤ የእኛ ድርሻ ራዕዩ በራሱ ጊዜ እስኪፈጸም ድረስ በተቀበልነው ራዕይ መንፈስ መኖር ብቻ ነው። አንዳንድ ጊዜ ከመጠን በላይ እንቅስቃሴ ስናበዛ ራዕዩን እንዘነጋዋለን። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የተሰጠንን ራዕይ በትዕግሥት አንጠብቅም። ወዲያና ወዲህ በሚያባክነን ሥራ ስለምንጠመድ ራዕዩ ሲፈጸም አናስተውለውም። ራዕዩ ሲዘገይ በትዕግሥት መጠበቅ ታማኝነታችን የሚለካበት ዋናው መመዘኛ ነው።

እግዚአብሔር በሕይወትህ የሚያመጣውን የዐውሎ ነፋስ ወቅት በጥንቃቄ አስተውል። በዚያ ዐውሎ ነፋስ አማካይነት እግዚአብሔር ቅዱሳኑን በተለያየ ቦታ ይተክላቸዋል። ምናልባት ቅጠሉ ያማረ ውስጡ ግን ምንም ፍሬ እንደሌለበት ዛፍ ሆነህ ትገኝ ይሆን? ፍሬያማ የምትሆነው ከእግዚአብሔር በተቀበልኸው ራዕይ መሠረት ስትኖር ብቻ ነው። እግዚአብሔር ከፈቀደ በወደደው ዐውሎ ነፋስ ውስጥ እስኪያሳልፍህ፣ በራሱ መንገድ እስኪያንቀሳቅስህ ደረስ ስፍራህን አትልቀቅ። እግዚአብሔር የተከለህ ተክል ከሆንህ ብዙ ፍሬ ታፈራለህ (ዮሐ. 15፣8)።

እግዚአብሔር በሰጠን ራዕይ «ብርሃን መመላለስ» ለሕይወታችን በጣም አስፈላጊ ነው (1ዮሐ. 1፣7)።

ሙሉ በሙሉ ሕይወትን መስጠት

«ጴጥሮስም፦ እነሆ፣ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ ደሰው ጀመር» (ማር. 10፣28)

ጴጥሮስ ሁሉንም ነገር የተወው ለምን እንደነበረ ጌታ ሲናገር «ስለእኔና ስለወንጌል» ነበር ያለው (10፣29)። ይህን ወይም ያንን እናገኛለን በማለት ደቀ መዛሙርቱ ላዘጋጁት ዓላማ አልነበረም ሁሉንም የተውት። ስለሆነም ጌታን የምትከተለው ለግል ጥቅም እንዳይሆን ራስህን መመርመር ይኖርብሃል። ሕይወታችንን ለጌታ የምንሰጠው ከኃጢአት እንዲያነጻን ወይም እንዲቀድሰን ሊሆን ይችላል። ከኃጢአት መንጻት ወይም መቀደስ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነታችንን የማስተካከል ውጤት ነው። ይሁን እንጂ ለእነዚህ ነገሮች ማለትም የኃጢአትን ስርየትና መቀደስ ሲባል ሙሉ በሙሉ ሕይወትን ለጌታ መስጠት ግን ክርስትና ከሚያስተምረው ጋር አይጣጣምም። ሕይወታችንን ለጌታ የምንሰጠው ምንም ዓይነት ጥቅም ፍለጋ አይደለም። ብዙ ጊዜ ግን የግል ጥቅማችንን ፈላጊዎች ስለሆንን ወደ እግዚአብሔር የምንመጣው ራሱን እግዚአብሔርን ፈልገን ሳይሆን ከእርሱ የምናገኘውን ጥቅም በመፈለግ ነው። ወደ እግዚአብሔር የምንመጣበት ዓላማ «ጌታ ሆይ፣ አንተን ሳይሆን የራሴን ምኞት መሟላት እፈልጋለሁ። የልቤን መሻት ከሰጠኸኝ በኋላም አንተ ያደረግኸውን ሰዎች እንዲያዩ እፈልጋለሁ» የሚል ዓይነት ይመስላል። ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ስንሰጥ መንግሥተ ሰማያትን፣ ከኃጢአት መንጻትንና ታላቅ የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆንን ማስቀደም የለብንም። ሙሉ በሙሉ ራሳችንን የምንሰጥበት ዓላማ ፈቃዱን በሕይወታችን እንዲፈጽም ለኢየሱስ ክርስቶስ ቅድሚያ ለመስጠት ነው።

ከእርሱ ጋር ያለን የዕለት ተዕለት ግንኙነት ምን ዓይነት ነው? ብዙዎቻችን ያለን አመለካከት «ጌታ ሆይ፣ ጥሪህን ሰምቻለሁ፣ ሆኖም የራሴ የሆነ ፍላጎት አለኝ፣ ለቤተሰቦቼም አስፈልጋቸዋለሁ፣ ከዚህ ርቄ ከአንተ ጋር መጓዝ አልችልም» የሚል ይመስላል (ሉቃ. 9፣57-62)። ኢየሱስ ደግሞ በዚህ ሁኔታ «ደቀ መዛሙርቴ ልትሆኑ አትችሉም» ነው የሚለው (ሉቃ. 14፣26-33)።

በእውነት ራሳችንን የሰጠን ከሆንን ግን ከዚህ የላቀ እርምጃ እንወስዳለን። ሕይወታችንን ለእግዚአብሔር ስንሰጥ በከፊል ወይም በጥቂቱ መሆን የለበትም። ብዙዎቻችን ይህን ቡተመለከተ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው ራዕይ ቢኖረንም ኖ በሚገ ራሳችንን አልሰጠንም።

እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ራሱን ለእኛ መስጠቱ

«ስግዚስብሔር... ስስኪሰጥ ደረስ ዓስሙን ስንዲሁ ወድዶስፊ» (ዮሐ. 3፣16)

ደኅንነት ስንል ከኃጢአት ነጻ መውጣትን ወይም የሕይወት መቀደስን ብቻ ማለታችን አይደለም። ከእግዚአብሔር የማገኘው ደኅንነት ሙሉ በሙሉ ከራሴ መውጣትን፣ ከእርሱም ጋር የጠበቀ ኅብረት ማድረግንም ያካትታል። ብዙ ጊዜ ስለደኅንነት ስናስብ ቶሎ ወደ አእምሮአችን የሚመጣው ከኃጢአት መላቀቅና ቅድስናን መለማመድ ቢሆንም፣ በመሠረቱ ግን ደኅንነት ከዚህ ላቅ ያለ ዓላማም አለው። በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ከራሱ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ኅብረትና ግንኙነት ሊኖረኝ ይገባል። ሙሉ በሙሉ ራሴን ለእግዚአብሔር ስሰጥ፣ ልቤ ከእኔ እጅግ በሚበልጠው ጌታ ላይ ይሆናል።

የተጠራነው ወንጌልን ወይም ቅድስናን እንድንሰብክ ነው የምንል ከሆነ ዋናውን ነጥብ ስተናል ማለት ነው፤ የተጠራነው ክርስቶስን እንድንሰብክ ነው (1ቆሮ. 2፣2)። ከኃጢአት መዳን ወይም የሕይወታችን መቀደስ እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ የመስጠቱ ውጤት ነው።

ሙሉ በሙሉ ራሳችንን የሰጠን ከሆንን በዚሁ ለመቀጠል ምንም የራሳችንን ጥረት አናደርግም። ጠቅላላ ሕይወታችን በእርሱ ውስጥ ይሆናል፣ እርሱም በእኛ ውስጥ ይሆናል። በዮሐንስ 3፣16 መሠረት እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ የመስጠቱ ምሥጢር ግልጽ የሚሆንልንም ያኔ ነው። እርሱ ሙሉ በሙሉ ራሱን እንደሰጠን ሁሉ እኛም ምንም ሳናስቀር ሙሉ በሙሉ ሕይወታችንን ለእርሱ እንሰጠዋለን። በዚህ ሁኔታ ራሳችንን ከሰጠን ደግሞ ጠቅላላ ሕይወታችን በእርሱ ውስጥ ስለሚሆን ምንም የሚያሰጋን ወይም የሚያሳስበን ነገር አይኖርም።

ተገዝተናል

«ለሰርሱ ለምትታዘዙለት ባሪያዎች እንደሆናችሁ አታውቁምን?» (ሮሜ 6፣16)

የገዛኝና በቁጥጥሩ ሥር ያደረገኝ ነገር ምን እንደሆነ ለማወቅ ራሴን በምመረምርበት ወቅት ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን ያለብኝ የመጀመሪያው ነገር ሕይወቴን የማስገዛት ኃላፊነት ያለብኝ መሆኑን ነው። ለእኔነቴ ባርያ ከሆንሁ፣ ተጠያቂው ራሴ እንጂ ማንም ሊሆን አይችልም፤ ምክንያቱም ራሴን ለእኔነቴ አስገዝቻለሁ ማለት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ለእግዚአብሔር እየታዘዝሁ ከሆነ፣ እኔነቴን ለእርሱ አስገዝቼአለሁ ማለት ነው።

አንድ ሰው ሁሉን ለእኔ ለሚል ጠባይ ከተገዛ የኋላ ኋላ ከማንኛውም ነገር ይልቅ ሊላቀቀው የማይችል ጨካኝ ጌታ ይሆንበታል። ከሰው ባሕርይ ውስጥ ከተገዛንለት ነገር ሊያላቅቀን የሚችል ምንም ዓይነት ኃይል የለም። አንድ ጊዜ ለአንድ ነገር ከተገዛችሁ ብትጠሉት እንኳ የዚያ ነገር ባሪያዎች ትሆናላችሁ። ይህ የተገዛችሁለት ነገር የሥጋ ምኞት ወይም የአእምሮ ዝንባሌ ሊሆን ይችላል። ከዚህ ዓይነት ባርነት ሊያላቅቃችሁ የሚችል የሰው ኃይል ሳይሆን ኢየሱስ መስቀል ላይ የፈጸመው የቤዛነት ሥራ ነው። ስለዚህ ሕይወታችሁን ከገዛው ነገር ሊያላቅቃችሁ ለሚችለው ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በፍጹም ትሕትና ራሳችሁን አስገዙ። እርሱ «ለተማረኩት ነጻነትን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛል» አለ (ሉቃ. 4፣18 እና ኢሳ. 61፣1)።

ለአንድ ነገር ከተገዛችሁ ያ ነገር ምን ያህል በእናንተ ላይ ኃይል ሊኖረው እንደሚችል ትረዳላችሁ፤ ምንም እንኳ አንድ ቀን ከዚህ ልማድ እላቀቃለሁ ብላችሁ ብታስቡም አይሆንላችሁም። ለዚያ ልማድ ተገዝታችሁለታልና ሕይወታችሁን ተቈጣጥሮታል። አንዳንድ ጊዜ «ተፈትቼአለሁ፣ ነጻም ወጥቻለሁ» እያልን እንዘምራለን፤ ሕይወታችን ግን የእኛነታችን ባርያ ሆኖአል። ይሁን እንጂ ለኢየሱስ ክርስቶስ ስትገዙለት ባርያ ካደረጋችሁ ከማንኛውም ነገር ነጻ ትሆናላችሁ።

ደቀ መዛሙርቱ ይደነቁ ነበር

«የተከተሉትም ደነገጡ ነበር» (ማር. 10፣32)

በመጀመሪያ ወደ ኢየሱስ በመጣንበት ጊዜ የእርሱ ተከታይ ስለመሆን ሁሉንም ነገር ያወቅን መስሎን ነበር። ለእርሱ ስንል ሁሉንም ነገር መተውና በፊቱ ራሳችንን መጣል ያስደስተን ነበር። በድፍረትም ለእርሱ ያለንን ፍቅር እንገልጽ ነበር። ውሎ ሲያድር ግን የነበረን እርግጠኛነት ሊጠፋ ይችላል። ኢየሱስ ቀድሞን ይሄዳል፤ ቀድሞ ከምናውቀው የተለየና የማይታወቅ ዓይነት ይሆንብናል። «ኢየሱስም ይቀድማቸው ነበርና ተደነቁ» (10፣32)።

አንዳንድ ጊዜ ኢየሱስ በጣም ለሚቀርቡት ደቀ መዛሙርት እንኳ እንግዳና ፈጽሞ የማያውቁት ሰው ይሆንባቸዋል። ቀድሞ የሚያውቁት ኢየሱስ ሳይሆን ፊቱ እንደ ባልጩቴት ይሆንባቸዋል (ኢሳ. 50፣7)። በማያወላውል ውሳኔ ወደፊት እየሄደ ነው። ስለሆነ መፍራትና መደናገጥ ሊኖር ይችላል። እንደ ቀድሞው የቅርብ ወዳጄና አጽናኜ መስሎ አይታየኝም። በዚህ ጊዜ ማድረግ ያለብኝ ዓይኔን በእርሱ ላይ ማድረግና በሚሆነው ነገር መደነቅ ብቻ ነው። በመጀመሪያ ያወቅሁትና የተረዳሁት መስሎኝ ነበር፤ አሁን ግን ያወቅሁ በመሰለኝ ነገር እንኳ እርግጠኛ አይደለሁም። በእኔና በኢየሱስ መካከል ርቀት በመኖሩም ከእርሱ ጋር በፊት በነበረኝ የቅርብ ግንኙነት መቀጠል አልቻልኩም። ወዴት እንደሚሄድ በእርግጠኝነት ማወቅ አልቻልኩም፣ መድረሻው ግብም ከጠበቅሁት በላይ ርቆአል።

በልቤ ያለው ኃጢአትና ጎዘን ለኢየሱስ መገለጥ አለበት፣ እንግዳና ያልተለመደ የሚሆንብኝም በዚህ ምክንያት ነው። በዚህ ጊዜ ነው እንግዲህ በፍጹም ኢየሱስን ገና እንዳላወቅኑው የምንረዳው። ባሕርዩንና ጠባዩን ገና አላወቅንም፤ እርሱን ስለመከተልም ገና በሚገባ አልተረዳንም፤ ፊት ለፊታችን ቀድሞ ሄዶአል፤ ያልተለመደና ወዳጃችን ያልነበረ ዓይነትም ሆኖብናል።

በዚህ ዓይነት የሕይወት ልምምድ ውስጥ በማለፍ ደቀ መዛሙርቱ ለሕይወታቸው በጣም የሚጠቅም ነገር መማር ነበረባቸው። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲገጥመን ትልቁ ችግራችን ግን ቆም እንልና ምናልባት ብርታት ይሆነን እንደሆነ በማለት ስላለፈ ሕይወታችን ማሰብ እንጀምራለን። ባለፈው ሕይወታችን ምን ያህል ታዛዥ እንደነበርን፣ ምን ዓይነት ትልቅ መሥዋዕት እንደከፈልን (ኢሳ. 1፣10-11 ይመለከቷል) እናሰላስላለን። ሆኖም እንዲህ ያለ የጨለማ ጊዜ ሲገጥመን እስኪያልፍ ድረስ በትዕግሥት እንጠብቅ፤ ምክንያቱም ከዚያ ጨለማ በኋላ በእውነት እርሱን የምንከተልበት ብርታት እናገኛለን፤ ይህ ደግሞ ከዚህ ቀደም አይተነው የማናውቀውን ደስታ ያስገኝልናል።

ጌታ ይፈርዳል

«ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና» (2ቆር. 5፣10)

ጳውሎስ እንደሚነግረን ሰባኪዎችም ሆንን ተራ አማኞች «በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንቀርባለን» ሆኖም እዚሁ እያለን በክርስቶስ ብርሃን ራሳችንን የምንመረምር ከሆነ በዚያ ቀን እፊቱ ስንቀርብ እርሱ በሕይወታችን ባደረገው ነገር ደስ ይለናል። ስለዚህም ሁልጊዜ ይህን የክርስቶስን ፍርድ ወንበር በሚያስብና እርሱ በሰጠን ቅድስና መረዳት እንኑር። ምንም ያህል የተቀደሰ ሕይወት ቢኖረንም ሌላውን ወንድማችንን የምንጠላ ከሆነ የምንኖረው በዲያብሎስ መንፈስ ነው ማለት ነው። በማንም ላይ ቢሆን እንድንፈርድ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። በሌላው ሰው ላይ ቅርታ ወይም ጥላቻ ቢኖርህ ወዲያውኑ በመናዘዝ ከልብህ አውጣው። እንደዚያ የማታደርግ ከሆነ ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ ልብህ እየደነደነና እየጠነከረ ይመጣል። ኃጢአት ከሚያስከትለው ፍርድ አንዱ ኃጢአትን አሜን ብለን መቀበል ነው። ኃጢአትን የሚቀጣው እግዚአብሔር ብቻ አይደለም፤ ኃጢአት ራሱ አድራጊውን ይቀጣል። ምንም ያህል ብትጸልይና የራስህን ጥረት ብታደርግም አንዳንድ ነገሮችን መተው ያዳግትህ ይሆናል፤ ያንን ነገር እየደጋገምህ ባደረግኸው መጠን ደግሞ ትለምደዋለህ፤ በመጨረሻም ኃጢአት መሆኑን እንኳ ከማትቀበልበት ደረጃ ላይ ትደርሳለህ። በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት ከሚገኘው ኃይል ውጪ ምንም ዓይነት ኃይል ኃጢአት ከሚያመጣው ውጤት ሊያላቅቅህ አይችልም።

«እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ...» (1ዮሐ. 1፣7)። ለብዙዎቻችን ግን በብርሃን መመላለስ ማለት በራሳችን መመዘኛና መስፈርት መሠረት መኖር ማለት ሆኗል። ትልቁ በደላችን እንደ ፈሪሳውያን በግብዝነት መኖራችን ሳይሆን ሳናውቀው በውሸት መኖራችን ነው።

የአገልጋዩ የመጀመሪያ ግብ

«... ዓላማችን እርሱን ደስ ማሰኘት ነው» (2ቆሮ. 5፡9 አ.መ.ት.)

ጳውሎስ «ዓላማችን...» ይላል። ምንጊዜም ቢሆን ዓላማችንና ግባችንን ፊት ለፊታችን ማኖር አለብን። ከፍተኛው የሕይወታችን ዓላማ ነፍሳትን ወደ ደህንነት ማምጣት፣ ቤተ ክርስቲያን መመሥረት ወይም ደግሞ መንፈሳዊ መነቃቃት እንዲኖር መጸለይ ሳይሆን ጌታን ማስደሰት መሆን አለበት። ለውድቀታችን ትልቁ ምክንያት መንፈሳዊ ልምምድ ማጣታችን አይደለም፤ ትልቁ ውድቀታችን ዓይኖቻችንን ትክክለኛው ዓላማ ወይም ግብ ላይ አለማድረጋችን ነው። እግዚአብሔር በሰጠን መስፈርት መሠረት መኖራችንን ለመመርመር ቢያንስ በየሳምንቱ ጊዜ ይኑረን። ጳውሎስ ከአድማጮቹ ጭብጨባ ወይም ምስጋና እንደማይጠብቅ ሙዚቀኛ ነበር፤ እርሱ የሚፈልገው የሙዚቃ መሪውን ምስጋና ብቻ ነበር።

ግባችን በእግዚአብሔር ፊት የማያሳፍር ሠራተኛ ሆነን መገኘት ሊሆን ይገባል፤ (2 ጢሞ. 2፣15) ከዚህ ግባችን በጥቂቱም እንኳ ቢሆን የሚያዘናጋን የራሳችን ዓላማ ካለን ግን እርሱ እንዳይጠቀምብን እንቅፋት ይሆንብናል። ያ ግብ ወዴት እንደሚያደርሰን በሚገባ ከተረዳን ደግሞ ዓይናችንን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ማድረግ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ግልጽ ይሆንልናል (ዕብ. 12፣2)። ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ እንዳይመራው ጳውሎስ እንኳ ራሱን መቈጣጠር አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል። «እኔ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ» ብሏል (1ቆሮ. 9፣ 27)።

ማንኛውንም ነገር ከዚህ ግብ ጋር በተያያዘ ሁኔታ መመልከት አለብኝ፤ ከዚህ ዓላማም እንዳልዘናጋ መጠንቀቅ ይኖርብኛል። በሕዝብ ፊት ማንነቴ የሚለካው በግል ከእግዚአብሔር ጋር በማሳልፈው ጊዜ መጠን ነው። ስለሆነም ትልቁ ግቤ እርሱን ማስደሰትና በእርሱ ፊት ተቀባይነትን ማግኘት ሊሆን ይገባል።

አስከዚህ ድረስ ለመምጣት ፈቃደኛ ነን?

«እግዚአብሔርን በመፍራት ቅድስናችንን ፍጹም እናድርገው» (2ቆሮ. 7፣1ስ.መ.ት)

«እንግዲህ ይህ ተስፋ ቃል ስላለን...» ተስፋዎቹ የእኛ መሆናቸውን እናውጃለን፤ ተስፋዎቹ እስኪፈጸሙ እንጠብቃለን፤ በመሠረቱ ይህን ማድረጋችን ትክክል ነው፤ ይህ ግን እኛ ለተስፋዎቹ ያለንን ግንባቤ ብቻ ነው የሚያመለክተው። ከእግዚአብሔር ዕይታ አንጻር ግን ከተስፋ ቃሎቹ የተነሣ እኛ የእርሱ መሆናችንን፣ በሕይወታችንም ጌታና ባለሥልጣን መሆኑን ያመለክታል። ታዲያ ሰውነታችን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መሆኑን ተረድተናል ወይስ በእግዚአብሔር ብርሃን ሲመረመር የምናፍርበትን ሥጋዊ ልማድ እያደረግን ነው? (1ቆሮ. 6፣14)። በቅድስና አማካይነት እግዚአብሔር የልጁን መልክ በእኔ ውስጥ አኑሮአል፤ በፊቱ ቅዱስ እንድሆን በማድረግም ከኃጢአት ለይቶኛል (ገላ. 4፣19)። ስለዚህም ሥጋዊ ሕይወቴ ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ይለወጥ ዘንድ ለእርሱ መታዘዝ ይኖርብኛል። በሕይወት ለሚገጥሙን ጥቃቅን ነገሮች እንኳ ሳይቀር እግዚአብሔር መመሪያ ሰጥቶናል። እግዚአብሔር በኃጢአትህ ሲወቅስህ ከሥጋና ከደም ጋር መመካከር ሳይሆን ቶሎ ብለህ ከኃጢአትህ መመለስ አለብህ (ገላ. 1፣16)። በዕለታዊ አኗኗርህ በየጊዜው ንጹሕ ሁን።

ከእግዚአብሔር ባሕርይ ጋር ፍጹም ኅብረት እንዲኖረኝ ሥጋዬና መንፈሴ ከማንኛውም ዓለማዊ ዕድፍ መቀደስ ይኖርባቸዋል። መንፈሴ በውስጤ ከሚኖረው ክርስቶስ ጋር ተስማምቶአል ወይስ በየጊዜው ያምጻል? የክርስቶስ አእምሮ ወይም ልብ ይኖረኝ ዘንድ ፈቃደኛ ነኝ? (ፈልጵ 2፣5)። ክርስቶስ በሁኔታዎች ሁሉ ለእግዚአብሔር ይገዛ ነበር እንጂ አንድ ጊዜ እንኳ ለመብቱ አልተከራከረም። የእርሱ መንፈስ በእኔ ውስጥ የሚኖር ከሆነ ደግሞ መንፈሴ ከመንፈሱ ጋር መስማማት ይኖርበታል። እንደዚያ ካደረግሁ ቀስ በቀስ ኢየሱስ መንፈሴን እርሱ ወደነበረበት ደረጃ ያነሣዋል፤ ያኔ ለምንም ነገር ግምት ሳልሰጥ ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛት እችላለሁ። ታዲያ እንዲህ ያለውን ቅድስና እግዚአብሔርን በመፍራት ፍጹም እያደረግሁ ነው? እግዚአብሔር ፈቃዱን በሕይወቴ እየፈጸመ ነው? ከበፊቱ በበለጠ ሁኔታ ሰዎች የእግዚአብሔርን ማንነት ከሕይወቴ እያዩ ነው?

ሌላውን ነገር ሁሉ በመተው ሕይወትህን ለእግዚአብሔር ለማስገዛት ቁርጥ ውሳኔ አድርግ። በማንኛውም ነገር በሕይወትህ ለእግዚአብሔር ቅድሚያ ስጠው።

የአብርሃም የእምነት ሕይወት

«...ወዴት እንደሚሄድ ባያውቅም እሺ ብሎ ሄደ» (ዕብ. 11፣8 ጴ.መ.ት)

በብሉይ ኪዳን ዘመን አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት የሚለካው ከሌሎች ነገሮች በተለየበት መጠን ነበር። ከአብርሃም ሕይወት የምንመለከተውም ይህንኑ ነው፤ አብርሃም ከአገሩና ከወገኖቹ ተለየ። በአሁኑ ዘመን ስለመለየት ስንናገር ግን እግዚአብሔርን ከማያውቁ ቤተሰቦቻችን በአካል እንለያለን ማለት ሳይሆን የሚያደርጉትን ባለማድረግ፣ እንደ እነርሱም ባለማሰብ እንለያቸዋለን ማለት ነው። በሉቃስ 14፣26 ኢየሱስ የሚናገረውም ስለ እንደዚህ ዓይነቱ መለየት ነው።

የእምነት ሕይወት ማለት ወዴት እንደምንመራ ሳናውቅ የሚመራንን ጌታ ማወቅና መውደድ ማለት ነው። የእምነት ጥሪ ምክንያታዊ መሆን አለመሆናችንን፣ መረዳት አለመረዳታችንን አይጠይቅም፤የሚጠይቀው የጠራንን ጌታ ማወቅ ብቻ ነው። የእምነት መሠረቱ እግዚአብሔርን ማወቅ ነው፤ ብዙ ጊዜ የምንሳሳተው ግን እምነት ካለን በዚህ ዓለም ሁሉም ነገር ይሳካልናል ብለን ስለምናስብ ነው።

የእምነት ሕይወት የመጨረሻው ደረጃ የባሕርይ ለውጥ ሲሆን፣ እዚህ ላይ ለመድረስ በተለያየ ሂደት እናልፋለን። በጸሎት ጊዜአችን የእግዚአብሔር መገኘት ይሰማናል፤ ይሁን እንጂ የምናገኘው ለውጥ ጊዜያዊ ነው፤ ወዲያውኑ ወደቀደመው አኗኗራችን ስለምንመለስ አብሮን የነበረው ክብር ይለየናል። የእምነት ሕይወት አልፎ አልፎ የምንለማመደው የተራራ ሕይወት ወይም በንስር ክንፎች መብረር ማለት ሳይሆን፣ ያለምንም መዛልና መታከት በየዕለቱ የምንኖረው ሕይወት ነው (ኢሳ. 40፣31)። እውነተኛነቱ ተፈትኖ የተረጋገጠለት የዕለት ተዕለት ኑሮ ነው። አብርሃም ተፈትኖ የተረጋገጠ እምነት እንጂ የቅድስና ምሳሌ መሆኑ አልተነገረንም። «አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ...» (ሮሜ 4፣3)።

አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ

«እግዚአብሔርም አለ፦ እኔ የማደርገውን ከአብርሃም ስሰውረውን?» (ዘፍ. 18፣17)

የእግዚአብሔር ወዳጅ መሆኑ ያስገኘለት ደስታ። ዘፍ. 18 የሚጀምረው የእግዚአብሔር ወዳጅ መሆን በሚያስገኘው ደስታ ነው። ማንኛችንም ብንሆን ስንጸልይ አልፎ አልፎም ቢሆን የእግዚአብሔር መገኘት ኃይል ይሰማናል፤ ይህ ዓይነት ወዳጅነት ግን በፍጹም የተለየ ነው። ይህ ዓይነቱ ወዳጅነት በጣም የጠበቀ ስለሚሆን አንድ ሰው እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ ፈቃዱን እንዲያሳየው እግዚአብሔርን መጠየቅ ላያስፈልገው ይችላል። ይህም አንድ ሰው ከፍተኛው የእምነት ሕይወት ላይ ለመድረሱ ዓይነተኛ ማስረጃ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ካለን ነጻነት፣ ደስታና መፈታት ይኖረናል፤ እኛ ራሳችን የእግዚአብሔር ፈቃድ እንሆናለን። የእግዚአብሔር መንፈስ ከመንፈስህ ጋር ግንኙነት ሲኖረው ማድረግ የሌለብህን ነገር ያመለክትሃል፤ ያ ካልሆነ ግን የምታስበውና የምትወስነው ሁሉ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የማይስማማ ይሆናል። ከእግዚአብሔር ጋር ካለህ ከዚህ የጠበቀና አስደሳች ግንኙነት የተነሣ በነጻነት ውሳኔዎችን ታደርጋለህ፤ የስሕተት ውሳኔ ለማድረግ ብትነሣሣ እንኳ በመንፈሱ አማካይነት ያስጠነቅቅሃል። እግዚአብሔር ሲያስጠነቅቅህ ደግሞ ወዲያውኑ እርምጃ መውሰድ ይኖርብሃል።

የአብርሃምና የእግዚአብሔር ወዳጅነት የገጠመው ችግር። አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው የጠበቀ ግንኙነት በመላላቱ መጸለይን እንዳቆመ እንመለከታለን፤ እንደ ቀድሞው የጠበቀ ግንኙነት ቢኖረው ኖሮ ግን የተመኘውን እስኪሰጠው ድረስ በጸሎት ይበረታ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ጸሎታችን የጠበቅነውን መልስ ሳያስገኝልን ሲቀር ምናልባት የእግዚአብሔር ፈቃድ ባይሆን ነው በማለት መጸለይን እናቋርጣለን። ኢየሱስ «እኔና አንተ አንድ እንደሆንን እነርሱም በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ» በማለት ጸልዮልን ነበር (ዮሐ. 17፣22)። ስትጸልይ ቅድሚያ የምትሰጠው ለማን ነው? የራስህ ምኞት እንኪፈጸም ወይስ ራሱን እግዚአብሔርን ለመፈለግ? አንዳንድ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለመቀበል ነው ወይስ ወደ እግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ? «ሳትለምኑት አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃል» (ማቴ. 6፣8)። ስለዚህ ለእግዚአብሔር ልመና የምታቀርብበት ዋናው ምክንያት ይበልጥ እግዚአብሔርን እንድታውቅና ይበልጥ ወደ እርሱ እንድትቀርብ መሆን አለበት። «በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ የልብህንም መሻት ይሰጥሃል» (መዝ. 37፣4)። እግዚአብሔር ራሱን በሚገባ እንድናውቅ ከተፈለገ ደግሞ ጸሎታችንን በአጭር ማቋረጥ የለብንም።

ከሞቱ ጋር ተባብረሃል ወይስ ስሜትህ ብቻ ነው የተነካው?

«ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ» (ገላ. 2፣20)

ማንኛችንም ብንሆን ልናረጋግጠው የሚገባን መንፈሳዊ ነገር ለአሮጌው ሕይወታችን መሞታችንን ነው። ለራሳችን አስተሳሰብና መብታችን ነው ለምንለው ነገር ሁሉ መሞት አለብን። ጳውሎስ «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ» ይላል። ክርስቶስን ለመምሰል ወስኜአለሁ ወይም እርሱን ለመከተል ጥረት አደርጋለሁ አላለም፤ በሞቱ ከእርሱ ጋር ተባብሬአለሁ ነበር ጳውሎስ ያለው። እዚህ ደረጃ ላይ ስደርስና በዚህ እውነት መሠረት መንፈሳዊ እርምጃ ስወስድ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የፈጸመው የቤዛነት ሥራ በሙሉ በሕይወቴ እውን ይሆናል። በዚህ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ራሴን ለክርስቶስ ከሰጠሁ ደግሞ ያለአንዳች መከልከል መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስን ቅድስና ይሰጠኛል።

«እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም...» እኔነቴ ወይም ግለሰብነቴ እንዳለ ይኖራል፣ ይሁን እንጂ ስገዛለት የኖርኩት የሕይወቴ ዓላማና ባሕርይ ሥርነቀል በሆነ ሁኔታ ይለወጣል። ሥጋዊ አካሌ ባይለወጥ እንኳ መብቴ ነው የምለው ነገር በአስደናቂ ሁኔታ ይለወጣል።

«አሁን በሥጋ የምኖርበት ኑሮ...» ሲል ሰዎች በሚያዩት በዚህ ሥጋዊ ሕይወቴ የምኖረው ኑሮ ማለቱ ነው። ይህ ሕይወት በእምነት የሚኖርበት ሕይወት እንደሆነ ሲናገር ደግሞ «በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ባለ እምነት የምኖረው ነው» ይላል። ይህ እምነት ጳውሎስ በራሱ ላይ ያለው እምነት ሳይሆን ከእግዚአብሔር ልጅ የተቀበለው ነው (ኤፌ. 2፣8)። ስለዚህ እምነት ስንናገር እምነትን በእምነት ላይ ማድረግ ማለታችን ሳይሆን፣ ወሰንና ገደብ ከሌለው ከእግዚአብሔር ልጅ ብቻ ስለሚገኝ እምነት መናገራችን ነው።

የሚቃጠል ልብ

«ልባችን ይቃጠል‌ብን ስለ‌ነበረ‌ምን?...» (ሉቃ. 24፣32)

ሠላንኛችንም ብንሆን ስለዚህ ስለሚቃጠል ልብ ምሥጢር መረዳት ይኖርብናል። ኢየሱስ ለነፍሳችን ግልጽ ሲሆንልን ነፍሳችን ውስጥ እሳት ይቀጣጠላል። አስደሳች ራዕዮችንም እንቀበላለን፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ የሚቃጠል ልባችን እንዳይቀዘቅዝ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል። በሁኔታዎች ውጣ ውረድ ውስጥ ማለፍ የሚችል እንዲህ ያለ ልብ ነው። በኢየሱስ የመኖርን ምሥጢር ካልተረዳን በቀር አታካች በሆነ የዕለት ተዕለት ውሎ የሚገጥሙን አስከፊ ሁኔታዎች ይህን የሚቃጠል ልባችንን ሊያቀዘቅዙብን ይችላሉ።

በክርስትና ሕይወታችን አብዛኞቹ ችግሮች የሚገጥሙን በምናደርገው ኃጢአት ሳይሆን የራሳችንን ባሕርይ ስለሚገዛው ሕግ ምንነት በሚገባ ባለመረዳታችን ነው። አንድ ዓይነት ስሜት በሕይወታችን እንዲኖር የምንፈቅድለት፣ በሚያስከትለው የመጨረሻ ወጤት መሠረት መሆን አለበት። የሚያስከትለው ውጤት እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ወይም እርሱ የማይፈቅደው ከሆነ ያ ስሜት በአስቸኳይ ከልባችን እንዲወጣ ማድረግ አለብን። ልብህን ያነሣሣው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ እርግጠኛ ከሆንህ ውጤቱ ምንም ይሁን ምን በምታደርጋቸው ውሳኔዎች ልትተማመንባቸው ትችላለህ። ሁልጊዜ በመለወጥ ተራራ ላይ ላንኖር እንችላለን (ማር. 9፣1-9) ይሁን እንጂ ከዚያ ባገኘነው ብርሃን መሠረት መኖር አለብን፤ ከዚያ ያገኘነውን መረዳት በሕይወታችን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርብናል። ከእግዚአብሔር ራዕይ ከተቀበልን የሚያስከፍለው ዋጋ የቱንም ያህል ቢሆንም ከእርሱ ጋር አንድ ዓይነት ውል በማድረግ በዚያ መሠረት መንቀሳቀስ አለብን።

አእምሮዬ ገና ሥጋዊ ነውን?

«ቅንዓትና ክርክር ስለሚገኝባቸው ገና ሥጋውያን መሆናቸሁ አይደለምን?...»

(1ቆሮ. 3፣3)

ተፈጥሮአዊ ወይም የማያምን ሰው ሥጋዊነት ምን ማለት እንደሆነ አያውቅም። ዳግም ስንወለድ ግን የሥጋ ምኞት በመንፈስ ፈቃድ ላይ ያምፃል፣ ሥጋ ከመንፈስ ጋር መንፈስም ከሥጋ ጋር ውጊያ ይገጥማሉ፣ እንግዲህ ሥጋዊነት ምን ማለት እንደሆነ በሚገባ የምናውቀው ያኔ ነው ማለት ነው። ይህን በተመለከተ ጳውሎስ ሲጽፍ «በመንፈስ ተመላለሱ፣ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ» ብሏል (ገላ. 5፣16)። በሌላ አነጋገር ሥጋዊነት መክሰም አለበት ማለት ነው።

በጥቃቅን ነገሮች ከሰዎች ጋር ትጋጫለህ? ወይም በቀላሉ ትረበሻለህ? ማንኛውም ክርስቲያን ነኝ የሚል ሰው እንደዚህ መሆን እንደሌለበት ታስባለህ? ጳውሎስ ግን እንደዚህ ዓይነት ክርስቲያኖች መኖራቸውን ነው የሚነግረን፣ ችግሩንም ከሥጋዊ አእምሮ ዝንባሌ ጋር ያያይዘዋል። መጽሐፍ ቅዱስን ስታነብ መንፈስህን የሚያስቄጣው ወይም ቅርታ እንዲያድርብህ የሚያደርግ እውነት አለ? እንደዚያ ከሆነ ገና ሥጋዊ ነህ ማለት ነው። በውስጥህ የተጀመረው ቅድስና ሂደት ቀጣይነት ቢኖረው ኖሮ ግን እንዲህ ያለ መንፈስ አይኖርህም ነበር።

መንፈስ ቅዱስ አንድን ስሕተት ቢጠቁምህም አንተው ራስህ ያንን ስሕተት እንድታስተካክል አይጠይቅህም፣ የሚጠይቅህ ነገር ቢኖር የእውነትን ብርሃን እንድትቀበል ነው፣ ከዚያ በኋላ እርሱ ችግሩን ያስተካክለዋል። የብርሃን ልጅ ኃጢአቱን ወዲያውኑ በመናዘዝ በእግዚአብሔር ፊት ነጻ ይሆናል። የጨለማ ልጅ ግን ይህን አይቀበልም። ብርሃን ሲበራልህና መንፈስ ቅዱስ ስለኃጢአት ሲወቅስህ እሺ በማለት የብርሃን ልጅ መሆንህን አሳይ፣ ኃጢአትህን ተናዘዝ፣ ያኔ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ያደርጋል። ራስህን ነጻ ለማውጣት ወይም በደለኛ አለመሆንህን ለማሳየት ሙከራ የምታደርግ ከሆነ ግን የጨለማ ልጅ መሆንህን እያስመሰከርህ ነው ማለት ነው።

ሥጋዊነት የመወገዱ ምልክት ምንድንነው? ራስህን ማሳሳት የለብህም፣ ሥጋዊነት ከሕይወትህ መወገዱ እውን ስለሚሆንልህ በሚገባ ታውቀዋለህ። የጸጋው ተአምር በሕይወትህ ያደረገውን የምታረጋግጥበትንም ዕድል እግዚአብሔር ያዘጋጅልሃል። በተግባር ተፈትኖ እውነተኛነቱ ስለሚረጋገጥ በፍጹም እንዲህ ያለ ነገር በሕይወቴ ሆኖ አያውቅም ትላለህ። በውስጥህ በተደረገው አስደናቂ ነገር አንተው ራስህ በጣም ትደነቃለህ፣ ትገረማለህ።

ለእርሱ ዓላማ ዝቅ ማለት

«ስርሱ ሲልቅ እኔ ግን ሳንስ ያስፈልጋል» (ዮሐ. 3፣30)

የሰዎችን ትኩረት ወደ ራስህ እየሳብህ ከሆነ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ነህ ማለት ነው። እንደ አገልጋይነትህ የአንተ ዋነኛ ኀላፊነት የሚዜነት ድርሻህን መወጣት ነው (3፣29)። የሕይወት ምሳሌነትህ አንድን ሰው በተገቢ ሁኔታ ወደ ክርስቶስ ጌትነት አምጥቶ ከሆነ፣ አገልግሎትህ ትክክለኛ ፈሩን ይዞአል ማለት ነው። ማንኛውም ሰው ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያለውን ግንኙነትና ኅብረት እንዲያጸርጥ የሚያደርግ ማንኛውንም ነገር እንዳታደርግ ተጠንቀቅ። ብዙ ግን እግዚአብሔር ብቻ ማድረግ ያለበትን ነገር በዚያ ሰው ሕይወት ለማድረግ እንሞክራለን። «ይህ ሰው በእንዲህ ያለ ችግር ማለፍ የለበትም» በማለት በዚያ ሰው ሕይወት ጣልቃ እንገባና የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳይፈጸም እንቅፋት እንሆናለን። የእኛ ድርሻ የሚዜነት መሆኑን እንዘነጋና የሙሽራውን ስፍራ ለመያዝ እንሞክራለን። አንድ ቀን ግን ያ ሰው ራሱ «ዓይኔን ከክርስቶስ ላይ አንሥቼ አንተ ላይ እንዳሳርፍ አድርገኸኛልና የማይገባህን ወስደሃል» በማለት ይወቅሰናል።

ምንጊዜም ቢሆን የሰዎች ደስታ ተካፋይ መሆን ያለብን ትክክል በሆነ ነገር እንጂ በተሳሳተ ነገር መሆን የለበትም። «ሚዜው ግን በሙሽራው ድምፅ ደስ ይለዋል። እንግዲህ ይህ ደስታዬ ተፈጸመ። እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል» (3፣29-30)። በመጨረሻ የሙሽራውን ሠርግ ለማየት በመብቃቱ ዮሐንስ ደስ አለው እንጂ አልከፋውም። ይህም ከመድረኩ ዘወር ማለትን ከሰዎች ዓይን ገለል ማለትን ይጠይቃል።

የሙሽራውን ድምፅ ከሌሎች ሕይወት በመስማትህ ደስ ሊልህ ይገባል። ይሁን እንጂ አንድን ሰው እዚህ ደረጃ ላይ ለማድረስ የተለያየ ውጣ ውረድ ጠይቆ ይሆናል። ምክንያቱም ጌታ አንድን ሰው ከማዳኑ በፊት ግለሰቡን በብዙ ሻካራ መንገድ ሊያሳልፈው ይችላል (ማቴ. 10፣34)።

ስፍራውን የጠበቀ ግንኙነት

«ሚዜው ግን በሙሽራው ድምፅ ደስ ደስ ይለዋል» (ዮሐ. 3፣29)

ዛሬ ግኤት ብረትን በሚስብበት ዓይነት መልካምነትና ንጽሕና ወደ ራሳቸው ሳይሆን የሰዎችን ትኩረት ወደ ክርስቶስ መሳብ ይኖርባቸዋል። ቅድስናዬ ሌሎችን ወደ ክርስቶስ መሳብ ካልቻለ ትክክለኛ ቅድስና አይደለም። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ የግል ሕይወቴ በሌሎች ላይ ያሳደረው ጫና ሊሆን ይችላል። የሰዎችን ፍላጎትና ስሜትም ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ ከመምራቱ በቀር የሚያመጣው ዘላቂ ለውጥ የለም። አንዳንድ ጊዜ ሰዎችን ወደ ራሱ ወደ ክርስቶስ ሳይሆን ክርስቶስ ወዳደረገው ወይም ወደሚያደርገው ነገር እንመራቸዋለን። አንዳንዶች ሕይወታችንን ተመልክተው ምን ዓይነት ጥሩ ሰው ነው? ሊሉን ይችላሉ፤ እንደዚያ ከሆነ ደግሞ የሚዜነት ድርሻችንን እያደረግን አይደለም ማለት ነው። ሚዜው «እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል» ለማለት መቻል አለበት።

ይህን የሚዜነት ተግባራችንን በሚገባ ለመወጣት ከምንም ነገር ይልቅ ከሙሽራው ጋር ስፍራውን የጠበቀ ግንኙነት ሊኖረን ይገባል። በመካከላችን ምንም ነገር ጣልቃ መግባት አስከማይችል ድረስ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያለን ግንኙነትና ጎብረት የጠበቀ መሆን አለበት። የጌታን ሥራ እያሠራን ነው እያልን ሰዎች ዓይኖቻቸውን ከእርሱ ላይ አንሥተው እኛ ላይ እንዲያሳርፉ አናደርጋለን። በራሱ መሣሪያ እርሱ አራሱ አንወጋለን።

ንጽሕናን በመጠበቅ መንፈሳዊ ራዕይ መቀበል

«ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው ስግዚአብሔርን ያዩታልና» (ማቴ. 5፣8)

ንጽሕና ጨዋነት ማለት አይደለም፤ ከዚያ የበለጠ ትርጥም አለው። ንጽሕና ከእግዚአብሔር ጋር ተስማምቶና ተጣጥሞ የመኖር ውጤት ነው። የሕይወት ንጽሕናችን በየጊዜው ማደግና መዳበር ይኖርበታል። ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ሕይወት ትክክል ሊሆን ይችላል፤ ውስጣዊ ንጽሕናችንም እንከን የሌለው ቢሆንም ውጫዊ ሕይወታችን ግን አንዳንድ ችግሮች ሊኖሩት ይችላል። የተሰጠንን መንፈሳዊ ራዕይ በንጹሕ ሕይወት የመጠበቅን አስፈላጊነት የምንማረው በዚህ መንገድ እንደሆነ ስለሚያውቅ እግዚአብሔር ውጫዊ ድካሞች እንዲኖሩን ይፈቅድ ይሆናል። ከእግዚአብሔር ጋር የምንኖረው ውጫዊ መንፈሳዊ ሕይወት አንድ ዓይነት ችግር ሲገጥመው ሌላውን ነገር ሁሉ ትተን ወዲያውኑ ማስተካከል አለብን። መንፈሳዊ ራዕይ ንጽሕናን እንደሚጠይቅ መዘንጋት የለብንም። ምክንያቱም «ልበ ንጹሖች እግዚአብሔርን ያዩታል» ነው ቃሉ የሚለው። ስለዚህም መንፈሳዊ ራዕይ ለመቀበል ንጽሕና አስፈላጊ ነው ማለት ነው።

በጸጋው አማካይነት እግዚአብሔር ያነጻናል፤ ይሁን እንጂ ያንን ንጽሕና ለመጠበቅ እኛም ማድረግ ያለብን ነገር ይኖራል። ብዙ ጊዜ የምንቆሽሸው በውጫዊ አካላችን ከተለያዩ ሰዎች ወይም ከተለያየ ዓይነት አመለካከት ጋር በምናደርገው ንክኪ ነው። ውስጣዊ ቤተ መቅደሳችን ብቻ ሳይሆን የመቅደሱ ውጫዊ አደባባይም በጸጋው አማካይነት እግዚአብሔር ከሚሰጠን ንጽሕና ጋር መጣጣም ይኖርበታል። ውጫዊው ነገራችን ሲቆሽሽ መንፈሳዊ ራዕያችንና ማስተዋላችንም ይደበዝዛል። ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያለንን ግንኙነትና ጎብረት ላለማበላሸት ስንል አንዳንድ የማናደርገው ወይም ማሰብ እንኳ የማይገባን ነገር ሊኖር ይችላል። ሌሎች የሚቀበሉት እኛ ግን የማንቀበለው ነገር ሊኖር ይችላል።

ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት ያማረ ሊሆን የሚችለው እግዚአብሔር በሚያያቸው ሁኔታ ስናያቸው ነው። ስለዚህም ይህ ወንድሜ ወይም ያች እኅቴ በኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ነው፤ ፍጹም ናት ለማለት መቻል ይኖርብናል።

ለግል ባሕርይ ጥንቃቄ በማድረግ መንፈሳዊ ራዕይ መቀበል

«ወደዚህ ሙጣና ከዚህ በኋላ ሲሆን የሚያስፈልገውን ነገር ስሳይሳሰሁ» (ሩዕ. 4፣1)

ከፍተኛ የአእምሮ ግንዛቤ ወይም የላቀ መንፈሳዊ ራዕይን መቀበል የምንችለው በግል ሕይወታችን ከፍተኛ የባሕርይ ልምምድ ባደረግን መጠን ነው። በተረዳኸውና በተገለጠልህ መሠረት ስትኖር ደግሞ እግዚአብሔር «ወዳጄ ሆይ፣ ወደዚህ ወደ ከፍተኛው ቦታ ና» ይልሃል። በፈተና ውስጥ ስትሆን ወደ ከፍተኛ ቦታ እንድትወጣ የሚያነሣህ የሚያቋርጥ ሕግ አለ፣ በምትወጣበት ጊዜ ግን ሌላ ፈተና ይገጥምሃል። እግዚአብሔርም ሆነ ሰይጣን ሰዎችን ወደ ከፍተኛ ስፍራ ያወጧቸዋል ሰይጣን የሚጠቀመው ግን በክፉ መንገድ ስለሆነ ውጤቱ በጣም የተለየ ነው። ሰይጣን ወደ ከፍተኛ ስፍራ ሲያደርስህ ሕይወትህ የመንፈሳዊ ዥዋዥዌ ሕይወት ይሆናል። ሚዛንህን ለመጠበቅ የተንጠለጠልህበትን ገመድ የሙጥኝ ብለህ ትይዛለህ፤ እንደ ልብህ ለመንቀሳቀስም ድፍረት አይኖርህም። በጸጋ አማካይነት እግዚአብሔር ወደ ሰማያዊ ስፍራ ሲያወጣህ ግን ያለምንም መሳቀቅ የምትረማመድበት ሰፊ ቦታ ታገኛለህ።

እስቲ የዚህ ሳምንት ሕይወትህን ካለፈው ዓመት ሕይወትህ ጋር በማወዳደር ምን ያህል እግዚአብሔር ወደ ከፍተኛ ልምምድ ደረጃ እንዳደረሰህ ለማሰብ ሞክር።ሁላችንም የተፈጠርነው ከከፍተኛ ደረጃ ላይ ሆነን ለማየት እንድንችል ነበር። በሕይወትህ የማትኖረውን ወይም ተግባራዊ የማታደርገውን እውነት እግዚአብሔር እንዲያሳይህ አትጠይቅ። ምን ጊዜም ቢሆን በተገለጸልህ እውነት መሠረት መኖር ይጠበቅብሃል።

በጸጋ ማደግህ የሚለካው ወደ ኋላ ባለመመለስህ ሳይሆን በመንፈሳዊ ሕይወትህ የት እንደሆንህ ተገቢ እይታና ማስተዋል ሲኖርህ ነው። ለመሆኑ እግዚአብሔር «ና ወደዚህ ውጣ...» ሲልህ ሰምተህ ታውቃለህ? ይህን ስል በሥጋዊ ጆሮህ ሳይሆን በውስጣዊ ሕይወትና ባሕርይህ ማለቴ ነው።

«እኔ የማደርገውን ከአብርሃም እሰውራለሁን?» አለ እግዚአብሔር (ዘፍ. 18፣17)። በየጊዜው በምናደርገው እድገት እርሱ ወዳለበት ደረጃ እስክንመጣ ድረስ ግን እግዚአብሔር የሚያደርጋቸውን ነገሮች ይሰውርብናል።

አለመግባባት ይኖር ይሆን?

«ከዚህም በኋላ ሰደቀ መዛሙርቱ ወደ ይሁዳ ደግሞ ስንሂድ ሰሳችሁ:: ስንርሱ ግን:- ..... ደግሞም ወደዚያ ትሂዳሰህን? ስሱት» (ዮሐ. 11፣7-8)

ኢየሱስ ክርስቶስ የሚናገረውን መረዳት ባለመቻሌ ብቻ ተሳስቶአል ወይም ትክክል አይደለም ለማለት መብት የለኝም:: ይህ አደገኛ አዝማሚያ ነው፤ እግዚአብሔር ለሚሰጠኝ መመሪያ በመታዘዜ ኢየሱስ ክርስቶስን አያስከብረውም ማለት አይደለም:: ኢየሱስ ክርስቶስን የማያስከብረው ለእርሱ መታዘዜ ብቻ አይደለም:: ምንም እንኳ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ውርደት እንደሚያስከትል ባውቅም እግዚአብሔር ከሰጠኝ መመሪያ ይልቅ የእኔን አስተሳሰብ ማስቀደምና እግዚአብሔር የነገረኝን አለማድርግ ትክክል አይደለም:: አንድ ነገር በጣም ከመደጋገሙ የተነሣ መመሪያዎቹ ከእግዚአብሔር እንደሆነ አውቃለሁ:: ይሁን እንጂ ጥቅምና ጉዳቱን ሳሰላስል ከእግዚአብሔር ያልሆነ ነገር ወደ አእምሮዬ እንዲገባ ፈቅጄለታለሁ ማለት ነው:: እንዲህ ካደረግሁኝ ደግሞ እግዚአብሔር የሰጠኝ ምሪት ትክክል አይደለም ማለቴ ነው:: ብዙዎቻችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ላለን አስተሳሰብ ታማኞች ነን፤ ለራሱ ለኢየሱስ ክርስቶስ ታማኝ የሆንንስ ስንቶቻችን ነን? ለኢየሱስ ታማኝ መሆን ማለት ምንም እንኳ የማየው ነገር ባይኖርም በእምነት እርምጃ መውሰድ ማለት ነው (ማቴ. 14፣29):: ለራሴ አስተሳሰብ ታማኝ መሆንን የምፈልግ ከሆነ ለዚያ ነገር አእምሮአዊ ምክንያት እፈልግለታለሁ ማለት ነው:: በመሠረቱ ግን እምነት ማለት በአእምሮ መረዳት ማለት ብቻ አይደለም፤ እምነት ምንም እንኳ ለዓይን የሚታይ ነገር ባይኖርም ሆን ብለንና ፈቅደን ራሳችንን ለኢየሱስ ክርስቶስ መስጠት ማለት ነው::

እርሱ የጠየቀህን ነገር ለማድረግ የእምነት እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ እንዴት ወይም መቼ እንደምታደርገው ክርክር ትገጥማለህን? ደስ ብሎሀ ለእርሱ ታዘዝ:: እርሱ አንድ ነገር ሲነግርህ የማትከራከር ወይም የምታመነታ ከሆነ የሚያስከብረውንና የማያስከብረውን ነገር ገና አልተረዳህም ማለት ነው:: ታማኝነትህ ለማንነው? ለኢየሱስ ክርስቶስ ወይስ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ላለህ አስተሳሰብ? እርሱ ለሚናገረው ነገር ታማኝ ነህ ወይስ ከእርሱ ያልሆነ አሳብን በማቅረብ ማወላወል ትፈልጋለህ? «የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ» (ዮሐ. 2፣5)::

ያልተጠበቀ የጌታ ጉብኝት

«ስኻነተ ደገሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ» (ሱቃ. 12፣40)

ክርስቲያን አገልጋይ የሚጠበቅ ትልቁ ነገር በማንኛውም መንገድና ሁኔታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ፊት ለፊት መገናኘት ነው። ያለፈ ዘመን ልምምዳችን ምንም ይሁን ምን ይህን ማድረግ ቀላል አይደለም። ውጊያው ከኃጢአት ወይም ከችግርና ከመከራ ጋር አይደለም፤ ውጊያው ኢየሱስ ክርስቶስን ለማገልገል ወዲያ ወዲህ ስንባክን ፊት ለፊት ከእርሱ ጋር ለመገናኘት ፈቃደኛ ከመሆን ወይም ካለመሆን ጋር ነው።

ብዙ ጊዜ ኢየሱስ ወደ እኛ የሚመጣው እኛ በጠበቅነው ቦታ ሳይሆን ባልጠበቅነውና ምክንያታዊ በማይመስል ሁኔታ ነው። ስለዚህ አንድ አገልጋይ ታማኝ መሆኑ የሚለካው ኢየሱስ በድንገት ሲመጣ ተዘጋጅቶ በመገኘቱ ነው። ይህ ዓይነት ዝግጅት የሚገኘው ደግሞ በአገልግሎት በመትጋታችን ሳይሆን መንፈሳዊ እውነታን በመቀበልና በማንኛውም ጊዜ እርሱን በንቃት በመጠበቅ ነው። በዚህ ሁኔታ ስንጠብቅ እንደ ሕፃን ሁሉ በጉጉትና በናፍቆት እንሞላለን። ኢየሱስ ክርስቶስን ስንጠብቅ ትልቁ ትኩረታችን ሃይማኖታዊ ነገሮች ላይ ሳይሆን መንፈሳዊ ሐቅ ላይ መሆን ይኖርበታል።

ትኩረትህን ከባዶ ሃይማኖታዊ አስተሳሰብ ላይ አንሥተህ ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ስታደርግ (ዕብ 12፣2)፣ ልብህን እርሱ በሚፈልገው ነገር ላይ ስታሳርፍ፣ የእርሱ አሳብ የአንተም አሳብ ሲሆን፣ ለአንዳንድ ሃይማኖት አክራሪዎች አጉል ሕልመኛና ከተግባራዊ ሕይወት የራቅህ ትመስላቸው ይሆናል። እርሱ በሚገለጥበት ጊዜ ግን ዝግጁ ሆነህ ትገኛለህ። ከእርሱ ይልቅ ለማንም ቅድሚያ መስጠት የለብህም፤ ምንም እንኳ እንደ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው የምትቈጥረው ቢሆንም፣ ዓይንህን ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እንዳታደርግ እንቅፋት ከሆነ ማንኛውንም ነገር ልታስወግደው ይገባል።

ቅድስና ወይስ ለእግዚአብሔር ልብን ማጠንከር?

«መደ ስርሱ የሚማሪድ ስንደሴስ ተረዳ፤ ተደነቀም...» (ሲሳ. 59፣16)

ብዙዎቻችን መጸለይን የምናቋርጠውና ለእግዚአብሔር ልባችንን የምናጠነክርበት ምክንያት ለጸሎት ያለን ፍቅር፣ ስሜት ሳይ በመመሥረቱ ነው። እንጸልያለን እንሳለን፤ ጸሎት ጠቃሚ መሆኑን፣ አእምሮአችንን እንደሚያረጋጋ፣ ነፍሳችንንም ወደ እግዚአብሔር እንደሚያቀና የሚናገሩ መጻሕፍትንም እናነባለን። ከዚህ ጥቅስ እንደምንመለከተው ግን ኢሳይያስ ስለጸሎት ባለን በእንዲህ ዓይነቱ አሳብ እግዚአብሔር እንደሚገረም እንደሚደነቅ ነው የሚነግረን።

ጸሎትና ለሌሎች መማለድ በፍጹም የማይነጣጠሉ ነገሮች ናቸው። መማለድ ለምንጸልይላቸው ሰዎች የክርስቶስ ልብ እስኪኖረን ድረስ ልባችንን ወደ እርሱ ማንሣት ማለት ነው (ፊልጵ. 2፣5)። እግዚአብሔርን ከማምለክ ይልቅ ጸሎታችን ማስኘንት ስላለበት ውጤት ለእግዚአብሔር ንግግር እናደርጋለን። «እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህን ነገር እንዴት እንደምታደርገው አላውቅም» ስንል እግዚአብሔርን እያመለክን ነው ወይስ ከእርሱ ጋር እየተከራከርን? እግዚአብሔር በሚገባ እያመለክን ላለመሆኑ እንዲህ ማለታችን ራሱ በቂ ማስረጃ ነው። ጥቂት የልመና ጸሎትን በእግዚአብሔር ፊት በማቅረብ ምን ማድረግ እንዳለበት ለእርሱ ልንነግረው እንሞክራለን። እንደዚህ የምናደርግ ከሆነ እግዚአብሔርን እያመለክን አይደለም፤ ልባችንም እንደ ክርስቶስ ልብ እንዲሆን ፍላጐት የለንም ማለት ነው። ልባችን፣ ለእግዚአብሔርና ለእርሱ ነገር ጠንካራ ከሆነ ደግሞ ለሌሎችም ጠንካራ ነው የምንሆነው።

በአምልኮ በምንሆንበት ወቅት እርሱ ወዳለበት ደረጃ መንፈሳችንን ከፍ ሲያደርገው ለምንጸልይላቸው ሰዎች የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ እንረዳለን። ታዲያ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ይህን ይመስላል ወይስ ገና ልባችን ለእግዚአብሔርና ለሌሎች ጠንካራ ነው?

በእውነተኛና በትክክለኛ መንገድ ለሕዝቡ የሚማልድ ሰው የለም በማለት ታስባለህ? እንግዲያውስ ለምን አንተ ራስህ ያ ሰው አትሆንም? ቅዱስ በሆነ ሁኔታ እግዚአብሔርን የምታመልክና ከእርሱም ጋር የተቀደሰ ግንኙነት ያለህ ሰው ሁን። ለሌሎች መማለድ ከባድ ሥራ ነው፤ ኃይልና ጉልበትህን የሚጠይቅ ሥራ ቢሆንም ምንም ዓይነት ስውር ተልዕኮ የለበትም። ሰዎች ወንጌልን ሲሰብኩ ስውር ዓላማ ሊናራቸው ይችላል፤ ለሌሎች መማለድ ግን በፍጹም ከዚህ የራቀ ነው።

ሌሎችን መርዳት ወይም ደንታ ቢስነት

«ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ነው፤... መንፈስ ስለቅዱሳን ይማልዳልና»

(ሮሜ 8፣34- 27)

መጽሐፍ ቅዱስ ስለክርስቶስ ሲናገር «ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና» ይላል (ዕብ. 7፣25)። ስለመንፈስ ቅዱስ ሲናገር ደግሞ «ስለቅዱሳን ይማልዳልና» ብሏል። ታዲያ እኛስ ለሌሎች ላለመማለድ የምናቀርበው ምክንያት ይኖረን ይሆን? ከመንፈስ ቅዱስ የተማርን የእግዚአብሔር ልጆች እንደ መሆናችን መጠን እኛስ ለሌሎች እንማልዳለን? ዙሪያችንና ያለንበትን ሁኔታ ረጋ ብለን እንይ፤ በቤታችን፣ በመሥሪያ ቤታችንና በህገራችን ወይም በሌላ ስፍራ ያሉ ችግሮች በጣም ተጫጭነውን ይሆን? ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔርን ለማምለክ እንኳ ጊዜ አጥተን ይሆን? እንደዚያ ከሆነ ሌላውን ነገር ሁሉ ትተን ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነትም ይስተካከላል፤ በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ተአምር ይሠራል።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ካለን ፍላጎት የተነሣ ከእርሱ ቀድመን እንዳንሄድ እንጠንቀቅ። ባሉን እቅዶችና እንቅስቃሴዎች ከእግዚአብሔር ቀድመን እንሄዳለን፤ የሌሎች ሸክም ስለተጫነንም እግዚአብሔርን በሚገባ አናመልክም፤ ለመማለድም ጊዜ አይኖረንም። እንደዚህ ከሆነ ደግሞ ልባችን ለእግዚአብሔር ጠንካራ ከመሆኑም ሌላ በነፍሳችን ውስጥ ተስፋ መቁረጥን ያኖራል። ሸክም ካላቸው የተለያዩ ሰዎች ጋር የሚያገናኘን እግዚአብሔር ነው፤ ይሁን እንጂ እርሱን የምናመልክ ካልሆነ ለሌሎችም ደንታ አይኖረንም። እንዲህ ያሉ ሰዎች ሲገጥሙን በችኩላ አንድ ወይም ሁለት ጥቅስ እንጠቅስላቸዋለን፤ ይህ ግን የቄሰለ ሰውን በጦር የመውጋት ያህል ሊሆን ይችላል፤ እኛ ራሳችን በሚገባ ያላሰብንበትን መንፈሳዊ ምክር በጥድፊያ እንሰጣቸዋለን። ጌታን በጣም የሚያሳዝነው ነገር ቢኖር የማያስብና የማያመዛዝን ክርስቲያን ነው።

ለሌሎች ለመማለድ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አብረን ለመማለድ እንድንችል ሕይወታችን በትክክለኛ ቦታ ነው ያለው?

ተወዳዳሪ የሌለው ክብር

«ጌታ ኢየሱስ ታዩ ዘንድ ሳከኝ» (የሐዋ. ፱፣17)

ጳውሎስ ሥጋዊ ዓይኑ በበራለት ጊዜ የኢየሱስ ክርስቶስንም ማንነት እንዲረዳ መንፈሳዊ ብርሃንንም ተቀብሎአል። ከዚያ ወዲህ ጠቅላላ ሕይወትና ስብከቱ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ብቻ ያተኮረ ነበር። «በመካከላችሁ ሳለሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር እርሱም እንደ ተሰቀለ ሌላ እንዳላውቅ ቆርጬ ነበርና» (1ቆሮ. 2፣2)። ከዚያን ጊዜ ወዲህ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ነፍስና አእምሮውን የሚስብ ምንም ዓይነት ነገር እንዲማርከው አልፈቀደም።

ከተቀበልነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ራዕይ ጋር የሚመጣጠን ጠንካራ ባሕርይን ማዳበር ይኖርብናል።

ከአንድ መንፈሳዊ ሰው የሚጠበቀው ትልቁ ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ በሕይወቱ ውስጥ ያለውን ስፍራ በሚገባ መረዳቱና የእግዚአብሔርንም ዓላማ ለሌሎች መግለጽ መቻሉ ነው። የሕይወቱ ናፍቆትና መሻት በሙሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ይሆናል። እንዲህ ያለ ሰው ከገጠመህ ያ ሰው እንደ እግዚአብሔር ልብ የሆነ ሰው እንደሆነ በእርግጠኝነት ልትናገር ትችላለህ (የሐዋ. 13፣22)።

ስለኢየሱስ ክርስቶስ ያለህን መረዳት ምንም ነገር እንዲያደበዝዘው ወይም አቅጣጫ እንዲያስለውጥህ አትፍቀድ። መንፈሳዊ መሆን ለጠሠህ የሚታወቀው በዚህ ነው። ሌሎች ነገሮች የሚማርኩህና የሚያጓጉህ አስከሆንህ ድረስ ግን የሚገባህን ያህል ገና መንፈሳዊ አልሆንህም ማለት ነው።

«ለሰላምሽ የሚሆነውን ብታውቂ»

ስለሰላምሽ የሚሆነውን በዚህ ቀን ስንቺ ስንኳ ብታውቂ ስሁን ግን ከዓይንሽ ተሰውሮአል (ሉቃ. 19፣42)

ኢየሱስ በድል አድራጊነት ወደ ኢየሩሳሌም ገብቶአል፤ ከተማይቱም ተረብሻለች፤ ነገር ግን በኢየሩሳሌም ከተማ የጠበቃቸው ጣዖት ነበር፤ የፈሪሳውያን ትዕቢት ነበር። ይህ ጣዖት መንፈሳዊና መልካም ይመስላል፤ ኢየሱስ ግን በወጭ አምሮ የሚታይ በውስጥ ግን አጥንትና ርኩሰት ከሞላበት መቃብር ጋር ነበር ያመሳሰለው (ማቴ. 23፣27)።

በዚህ ቀን ለእግዚአብሔር ሰላም ዓይናችንን ያሳወረው ነገር ምን ይሆን? ምናልባት ያማረ የሚመስል፣ በእግዚአብሔር ፊት ግን ርኩስና ጸያፍ የሆነ ጣዖት ሕይወታችንን ተቆጣጥሮት ይሆን? ከአንድ ጊዜ በላይ እግዚአብሔር በሕይወቴ ውስጥ ያለውን ጣዖት አመልክቶኝ ነበር፤ ከዚህ ጣዖት መላቀቅ እንዳለብኝም ይገባኝ ነበር፤ ሆኖም እንደዚያ አላደረግሁም። የራሴን ጥረትና ሙከራ ባደርግም ከዚያ ጣዖት አልተላቀቅሁም፤ ለሰላሜ ለሚሆነው ነገር ዓይኔ ታውሮአል። ከአንድ ጊዜ በላይ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለምንም መከልከል የሚሠራበት ቦታ ላይ ነበርን፤ ሆኖም ይበልጥ ነገሮችን በማወሳሰብ በእግዚአብሔር ፊት በደለኞች ሆነናል።

«ብታውቂ» የሚለው ቃል ለራሳችን ጥፋት ኀላፊነት እንዳለብን ያመለክታል። በኃጢአታችን ምክንያት ለተጋረደብን ወይም ደግሞ ማየት ላልፈለግነው ነገር እግዚአብሔር ቡኀላፊነት ይጠይቀናል። ዓመፀኛ ተፈጥሮአችንን ለእርሱ ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆናችን ለሰላማችን የሚሆነው ነገር ከዓይናችን ይሰወራል። «...አሁን ግን ከዓይንሽ ተሰውሮአል» እንደዚያ ባይሆን ኖሮ ሁኔታዎች ምንኛ የተለዩ መልክ ይኖራቸው ነበር! በኃጢአታችን ምክንያት የተዘጋብን በር ምናልባት ለሁለተኛ ጊዜ ላይከፈት ይችል ይሆናል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሌላ በር ይከፍታል፤ ባለመታዘዛችን ምክንያት መዘጋት ያልነበረበት በር እንደተዘጋ ግን ሲያሳስበን ይኖራል። እግዚአብሔር ያለፈ ዘመን ሕይወታችንን ሲያመለክተን ወይም ሲያሳስበን በፍጹም መደንገጥ የለብንም። ያም ሆኖ ካለፈ ሕይወታችን የተማርነውን መዘንጋት የለብንም። ምናልባትም ይህን የሚያደርገው በተለያዩ አገልጋዮች አማካይነት ሊሆን ይችላል፤ ለወደፊት ሕይወታችን እድገት የሚሆን ትምህርት ስለምናገኝበት በደስታ እንቀበለው።

የዘላቂ እምነት መንገድ

«ስደንዳንዳችሁ የምትበታተኑበት ሰዓት ይመጣል» (ዮሐ. 16፣32)

ኢየሱስ ይህን የተናገረው ደቀ መዛሙርቱን ለመገሠጽ አልነበረም። በዚህ ወቅት ደቀ መዛሙርቱ እውነተኛ እምነት ነበራቸው፤ ይሁን እንጂ ሥርዓት ያልያዘና ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ ያነጣጠረ አልነበረም፤ አስፈላጊ በሆኑ በሕይወት እውነታዎች ላይ የመሥራት አቅም አልነበረውም። በየግል ወደሚያሳስባቸው ነገር ተበታትነዋል፤ ከኢየሱስ ክርስቶስ ውጪ የሆነ የየግላቸው ጉዳይ ነበራቸው። በመንፈስ ቅዱስ የመቀደስ ኃይል አማካይነት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ካስተካከልን በኋላ በየዕለቱ በሚገጥሙን የሕይወት እውነታዎች እምነታችን መሥራት ይኖርበታል። አንዳንድ ጊዜ ግን ለአገልግሎት ሳይሆን ወደ ባዶነትና የፍሬቢስነት ሕይወት ምን እንደሚመስል ወደምንማርበት ሁኔታ እንበተናለን። ለዚህ ተዘጋጅተን ይሆን? ይህ ሁኔታ በምርጫችን የምናደርገው አይደለም፤ ነገሮችን ሁሉ እየመራና እየተቈጣጠረ ወደዚህ ሁኔታ የሚያደርሰን እግዚአብሔር ራሱ ነው። በዚህ ልምምድ እስካለፍንበት ጊዜ ድረስ እምነታችን የተመሠረተው ደስ በሚያሰኙ ስሜቶቻችንና በምናገኘው ባርኮት ነበር። አንድ ጊዜ እዚህ ልምምድ ውስጥ ከገባን ግን የቱንም ያህል የባዶነትና የፍሬ ቢስነት ሕይወት ቢሆንብንም ስለማንኛውም ነገር እግዚአብሔርን የማመስገን አስፈላጊነትን እንማራለን። በዕለታዊ የሕይወት እውነታዎች የሚሠራ እምነት ማለትም ይኸው ነው።

«እኔንም ለብቻዬ የምትተዉበት ሰዓት ይመጣል» የሚያደርግልንን ጥበቃና ጥንቃቄ በመዘንጋት ኢየሱስን ብቻውን ትተን የተበተንበት ሁኔታ ገጥሞን ያውቃል? ታዲያ በዚያ ውስጥ እንኳ እግዚአብሔር ሲሠራ አላየንም?አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በሉዓላዊ ሥልጣኑ አማካይነት በጨለማ ወቅት እንድናልፍ ይፈቅዳል። እግዚአብሔር በሕይወታችን የፈለገውን እንዲያደርግ ፈቃደኞች ነን? ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ የሕይወታችን ጌታ ካልሆነ በቀር የየግላችን ፍላጎትና ግብ ይኖረናል። እምነታችን እውነተኛና ትክክል ነበር፤ ሆኖም ቀጣይና ዘላቂ አልነበረም። እግዚአብሔር በፍጹም አይቸኩልም፤ አይጣደፍም። እርሱን በትዕግሥት ከጠበቅነው ለእርሱ ያልተገዛ ነገራችንን ያመለክተናል፤ ትልቁ ትኩረታችን ከእርሱ የምንቀበለው በረከት ላይ እንጂ እርሱ ራሱ ላይ አለመሆኑን ያመለክተናል።

«ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፈዋለሁ» (ዮሐ. 16፣33)። የሚያስፈልገን በሁኔታዎች የማይናወጥ መንፈሳዊ ጽናት ነው።

በእርሱ ጣዕር ወደ እግዚአብሔር መግባትን አገኘን

«ጲዮሱስ ከእነርሱ ጋር ጌቴሴማኒ ወደምትባል ስፍራ መጣ ደቀ መዛሙርቱንም በዚህ ቁዩ ከእነም ጋር ተጉ ስሳቸው» (ማቴ. 26፣36,38)::

በጌቴሴማኒ በኢየሱስ ላይ የደረሰበትን ጣዕር በፍጹም በሚገባ መረዳት አንችልም፤ ያም ሆኖ ግን ቢያንስ በተሳሳተ መንገድ መረዳት የለብንም:: ጌቴሴማኒ በኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔርና ሰው ፊት ለፊት የተፋጠጠየበት ቦታ ነው:: በግል ሕይወት ልምምዳችንም ቢሆን የጌቴሴማኒን ጣዕር መረዳት አንችልም:: ጌቴሴማኒና ጎልጎታ ፍጹም ልዩ የሆነ ነገርን ነው የሚወክሉት:: ወደ ሕይወት የምንገባው በዚህ በር ነው::

ኢየሱስን በጌቴሴማኒ ያሳሰበው መበቀል ላይ መሞቱ አልነበረም:: እርሱ ወደዚህ ዓለም የመጣው ለመሞት መሆኑን ደግሞ ደጋግሞ ተናግሮ ነበር:: ኢየሱስን በጣም ያሳሰበው ነገር በዚህ ትግል እንደ ሰው ልጅነቱ እንዳይሞት ነበር:: ኢየሱስ የመጣው እንደ እግዚአብሔር ልጅነት ለመሞት ነበር፤ የሰይጣን ዓላማ ግን ኢየሱስ እንደ ማንኛውም ሰው እንዲሞት ነበር:: ኢየሱስ እንደ ሰው ልጅነቱ ብቻ ቢሞት ኖሮ ደግሞ አዳኛችን መሆን ባልቻለም ነበር (ዕብ. 9፣11-15):: በተጨማሪም ከዚህ ቀደም የጌቴሴማኒ ጣዕሩን በምድረ በዳ ከገጠመው ፈተና አንጻር ልንመለከተው ይገባል:: «ዲያብሎስም ፈተናውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ እስከ ጊዜው ከእርሱ ተለየ» ይላል (ሉቃ. 4፣13):: በኋላ ግን ዲያቢሎስ ጊዜውን ጠብቆ ኢየሱስን ለመፈተን ጌቴሴማኒ ቢመጣም እቅዱ አልተሳካለትም:: ዲያብሎስ እንደ ሰው ልጅነቱ ኢየሱስን ለመጨረሻ ጊዜ የተፈታተነው በጌቴሴማኒ ነበር::

የጌቴሴማኒ ጣዕር እንደ ዓለም አዳኝነቱ የእግዚአብሔር ልጅ የተቀበለው መከራ ነበር:: እኛ የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆን የከፈለው ዋጋ ምን ያህል ታላቅ እንደ ነበር በግልጽ የታየው በዚሁ ስፍራ ነበር:: ለሁላችንም መዳን የሆነልን ከዚህ ጣዕር የተነሣ ነው:: የክርስቶስ መስቀል የሰው ልጅ ድል የተቀዳጀበት ነው:: ኢየሱስ ከከፈለው ቤዛነት የተነሣ እኛ ወደ እግዚአብሔር ፊት መቅረብን አገኘን::

የእግዚአብሔርና ኃጢአት ፊት ለፊት መጋጨት

«እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ» (1ጴጥ. 2፣24)::

የክርስቶስ መስቀል እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ፍርዱን ወይም ቅጣቱን የገለጸበት እውነት ነው:: የኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞት እንደ ማንኛውም ሰማዕት ዓይነት ሞት አልነበረም፤ ከዚህ የተሳሳተ አዝማሚያ መጠንቀቅ ይኖርብናል:: ሞቱ ታላቅ ድል በመሆኑ የገሃነም መሠረትን አነቃንቆአል:: በዚህ ዓለምም ሆነ በዘላለማዊው ዓለም ክርስቶስ በመስቀል ላይ የፈጸመውን ሥራ የሚያስተባብል ምንም ዓይነት ኃይል ሊኖር አይችልም፤ የሰው ልጆች በሙሉ ከእግዚአብሔር ጋር ጎብረት ማድረግ የቻሉት በክርስቶስ ሞት ነው:: የሰው ልጆች መዳን መሠረትም የክርስቶስ መስቀል ነው::

የክርስቶስ ሞት ድንገተኛ አጋጣሚ አልነበረም፤ መጀመሪያውኑ እርሱ የመጣው በመስቀል ላይ ለመሞት ነበር:: እርሱ «ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ የታረደ በግ» ነው (ራዕ. 13፣8):: ያለ መስቀሉ የክርስቶስ በሥጋ መገለጥ ብቻውን ምንም ትርጉም ሊኖረው ባልቻለም ነበር:: «እግዚአብሔር በሥጋ ተገለጠ» የሚለውን እውነት «ስለእኛ ኃጢአት አደረገው» ከሚለው ነጥለን ልንመለከተው አይገባም (1ጢሞ 3፣16, 2ቆሮ. 5፣21):: የክርስቶስ በሥጋ መገለጥ ዓላማ የቤዛነቱ ሞት ነው:: እግዚአብሔር በሥጋ የተገለጠው ኃጢአትን ለማስወገድ እንጂ ለራሱ የሚያስገኘው ጥቅም ስለነበር አይደለም:: መስቀል በጊዜና በዘላለም መካከል ያለ ድርጊት ነው፤ በጊዜም ሆነ በዘላለም ለሚኖር ችግርም መልስ ነው::

መስቀሉ የእግዚአብሔር እንጂ የሰው አይደለም፤ የሰው ልጅ በልምምዱ ሊረዳው የማይችለውም በዚህ ምክንያት ነው:: መስቀሉ እግዚአብሔር ባሕርዩን የገለጸበት ነው:: የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሚሆነውም መስቀል ላይ ከተፈጸመው ቤዛነት የተነሣ ነው:: ይሁን እንጂ ይህ ልምምድ አንድ ጊዜ ብቻ የምናልፍበት ሳይሆን በዚህ ምድር እስካለን ድረስ ሁሉ የምንኖርበት ነው::

የደኅንነታችን ማዕከል የክርስቶስ መስቀል ነው:: ማንኛችንም ብንሆን ደኅንነትን የምናገኘው እግዚአብሔር ከከፈለው ክቡር ዋጋ የተነሣ ነው:: መስቀሉ የሕይወት በር የተከፈተበት ነው::

የመረዳት ጉድለት

«ከተራራውም ሲወርዱ የሰው ልጅ ከሙታን እስኪነሣ ድረስ ያዩትን ሰማንም እንዳይነገረ አዘዛቸው» (ማር. ፱፣፱)

ቅ መዛሙርቱ እንደታዘዙት ሁሉ ክርስቶስ በሕይወትህ እስኪነሣ ድረስ፣ የትንሣኤው ኃይል ሕይወትህን እስኪቈጣጠርና የእርሱን ትምህርት መረዳት እስክትችል ድረስ እርሱን በተመለከተ ምንም ነገር ማውራት የለብህም። በሕይወትህ ስታድግና ውስጣዊ ነገርህም ሲስተካከል ከዚህ ቀደም ለምን መረዳት እንዳልቻልህ እስኪደንቅህ ድረስ ኢየሱስ የተናገረው ግልጽ ይሆንልሃል። የክርስቶስን ንግግር ወይም ትምህርት መረዳት ያልቻልከው ትክክለኛውን መንፈሳዊ ሕይወት ባለማዳበርህ ነበር።

እነዚህን ነገሮች መረዳት ያልቻልነው ጌታ ስለሰወረብን አልነበረም፤ መረዳት ያልቻልነው መንፈሳዊ ሕይወታችን ባለማደጉ ልንቀበላቸው ስላልቻልን ብቻ ነበር። ኢየሱስ «የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፣ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም» አለ (ዮሐ. 16፣12)። ከእርሱ አንድን እውነት ለመቀበል ከመዘጋጀታችን በፊት ከትንሣኤው ሕይወት ጋር መተባበር ይኖርብናል። በውስጣችን ስላለው የኢየሱስ ትንሣኤ ሕይወት የተረዳነው ነገር ይኖረን ይሆን? ይህ ለመሆኑ ዋናው ማስረጃ ቃሉን መረዳታችን ነው። መንፈሱ ከሌለን በቀር እግዚአብሔር ምንም ነገር አይገልጽልንም። ያልተገዛ ሕይወታችንና ለዘመናት የያዝነው የራሳችን አሳብ እግዚአብሔር አንድን ነገር እንዳይገልጥልን ዋናው እንቅፋት ነው። የትንሣኤው ኃይል በሕይወታችን መሥራት ሲጀምር ግን እንቅፋት የሆነብን የራሳችን አስተሳሰብና አመለካከት እየከሰመ ይሄዳል።

«ለማንም እንዳይነግሩ አዘዛቸው» ብዙዎች ስለተራራው ሕይወት ልምምዳቸው ብዙ ያወራሉ። እርግጥ ነው እነዚህ ሰዎች ያዩት ራዕይ ይኖራቸዋል፤ አየን የሚሉትና የሚኖሩት ግን እርስ በርሱ ይጋጫል። የእግዚአብሔር ልጅ በትንሣኤው ኃይል በውስጣቸው ስላልተገለጠ ሕይወታቸው ፍሬ የለውም። የትንሣኤው ኃይል በእኔና በእናንተ ሕይወት እስኪታይ ድረስ ምን ያህል ጊዜ እንቆይ ይሆን?

የትንሣኤው ፍጻሜና ግብ

«ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደ ክብረ ይገባ ዘንድ ይገባው የሰምን?» (ሉቃ. 24፣26)

ጌታ መስቀል ወደ እርሱ ሕይወት የምንደርስበት በር ነው። የእርሱን ሕይወት ለእኔ የሚያስተላልፈው ደግሞ በትንሣኤው ኃይል አማካይነት ነው። ዳግም በተወለድሁበት ጊዜ ከሞት የተነሣውን የኢየሱስን ሕይወት ተቀብዬአለሁ።

የክርስቶስ ትንሣኤ ዓላማ በእግዚአብሔር በተወሰነው መሠረት «ብዙ ልጆችን» ወደ ክብር ማምጣት ነው (ዕብ. 2፣10)። በትንሣኤው በኩል እኛን የእግዚአብሔር ልጆች የማድረግ መብት አግኝቶአል። ልክ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር እንዳለው ዓይነት ግንኙነት አይኖረንም፤ ይሁን እንጂ በልጁ አማካይነት የእግዚአብሔር ልጆች ወደምንሆንበት ጎብረት እንደርሳለን። ጌታ ከሞት የተነሣው በሥጋ ከተገለጠ በኋላ ወዳልነበረው አዲስ ሕይወት ነው። በትንሣኤው አማካይነት እኛም ወደዚሁ የክርስቶስ ትንሣኤ ሕይወት እንጂ ወደ አሮጌው ሕይወታችን አይደለም የምንነሣው። አንድ ቀን ደግሞ የእርሱን ዓይነት ክቡር አካል እንለብሳለን፤ እስከዚያ ድረስ ግን «በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ» የትንሣኤው ኃይል በሕይወታችን ይሠራል (ሮሜ 6፣4)። ከፍተኛው የጳውሎስ ዓላማና ግብ «እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል አውቅ ዘንድ» የሚል ነበር (ፊልጵ. 3፣10)።

«በሥጋም ሁሉ ላይ ሥልጣን እንደ ሰጠኸው ለሰጠኸው ሁሉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸው ዘንድ» በማለት ኢየሱስ ጸልዮአል (ዮሐ. 17፣2)። መንፈስ ቅዱስ የሚለው አገላለጽ በዚህ ሕይወት እያለን በእኛ ውስጥ የሚሠራው የዘላለም ሕይወት ልምምድ ሌላው መጠሪያው ነው ለማለት ይቻላል። የክርስቶስን መስቀል ቤዛነት ኃይል በሕይወታችን እንዲሳል የሚያደርግ መንፈስ ቅዱስ ነው፤ ይህ እንዲሆን ደግሞ መታዘዝ ይኖርብናል።

በእምነት ዓይኖችህ ኢየሱስን አይተሃልን?

«ከዚህም በኋላ ከእነርሱ ለሁለቱ በሌላ መልክ ተገለጠ» (ማር. 16፣12)

ዐዳን ማለትም ደኅንነትን ማግኘትና ኢየሱስን ማየት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ኢየሱስን ያላዩ በጣም ብዙ ሰዎች አሉ፤ ይሁን እንጂ የእግዚአብሔርን ጸጋ ተቀብለዋል፤ የጸጋው ተካፋዮችም ሆነዋል። አንድ ጊዜ ኢየሱስን ካየን ግን ሕይወታችን በፍጹም እንደ ቀድሞው አይሆንም እንደ ከዚህ ቀደሙ ሌሎች ነገሮች አይማርኩንም።

ምንጊዜም ቢሆን ኢየሱስን በማየትና እርሱ ያደረገልንን ነገር በመረዳት መካከል ያለው ልዩነት ግልጽ ሊሆንልን ይገባል። እርሱ ያደረገልንን ብቻ የምናይ ከሆነ የሚገባውን ያህል በትልቅነቱ አላየነውም ማለት ነው። ልምምዶች ይመጣሉ ይሄዳሉ፤ አንድ ጊዜ ስለኢየሱስ ማንነት ራዕይ ካገኘህ ግን የማይታየውን አይተሃልና በምንም ነገር አትናወጥም (ዕብ. 11፣27)። ከተወለደ ጊዜ ጀምሮ ዕውር የነበረው ሰው ክርስቶስ ራሱን እስከ ገለጠለት ጊዜ ድረስ አላወቀውም ነበር (ዮሐ. 9)። አንዳች ነገር ላደረገላቸው ወገኖች ኢየሱስ ራሱን ይገልጥላቸዋል፤ መቼ እንደሚገለጥላቸው የሚወስኑት ግን እነርሱ አይደሉም። እርሱ በፈቀደው ጊዜ ራሱን መግለጥ ይችላል። ያኔ «... ዐይነ ስውር እንደነበርሁ አሁን ግን እንደማይ ይህን አንድ ነገር አውቃለሁ» (ዮሐ. 9፣25አ.መ.ት) በማለት በመደነቅ እንጮኻለን።

ለአንተም ሆነ ለቅርብ ወዳጅህ በየግላችሁ ኢየሱስ ሊገለጥላችሁ ይችላል፤ ማንም በአንተ ዓይን ኢየሱስን ማየት አይችልም። አንተም ብትሆን በሌሎች ዓይን ልታየው አትችልም። መለያየት የሚመጣው እዚህ ላይ ነው፤ አንዱ አይቶታል ሌላው ግን አላየውም። አንተ ያየኸውን ሌላው እንዲያይ ማድረግ አትችልም፤ ያን የሚያደርግ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ኢየሱስን አይተኸዋልን? ኢየሱስን አይተህ ከሆነ ሌላው እንዲያየው መፈለግህ የማይቀር ነው። «እነርሱም ሄደው ያዩትን ለሌሎች አወሩ፤ እነዚያንም ደግሞ አላመኑአቸውም» (ማር. 16፣13)። በእርግጥ እርሱን አይተህ ከሆነ ባያምኑህም እንኳ ለሌሎች መናገር ይኖርብሃል።

ኃጢአትን በተመለከተ ቆራጥና የማያወላውል ውሳኔ

«ከእንግዲህ ወዲህ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ እርፈሙ ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን» (ሮሜ 6፣6)

ከኢየሱስ ጋር መሰቀል። በውስጥህ ያለው ኃጢአት እንዲሞት የማያወላውል ውሳኔ ላይ ደርሰሃልን? ኃጢአትን በተመለከተ እንዲህ ያለ ቆራጥና የማያወላውል ውሳኔ ላይ ለመድረስ ምናልባት ረጅም ጌዜ ሊወስድ ይችላል። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ለዓለም የተሰቀለበት መስቀል ላይ ኃጢአትህም እንዲሰቀል የምታደርገው ውሳኔ በሕይወት ዘመንህ ሁሉ ስታስታውሰው የምትኖረው ጊዜ ነው። ማንም ቢሆን ሌላውን ሰው እዚህ ውሳኔ ላይ ሊያደርሰው አይችልም። የተሟላ አእምሮአዊና መንፈሳዊ መረዳት ሊኖረን ይችላል፤ ነገር ግን በዚህ ብቻ ሳንወሰን በዚህ ምንባብ ጳውሎስ ወደሚያቀርብልን ጥሪ ለመድረስ ውሳኔ ማድረግ ይኖርብናል።

ራስህን ከሌሎች ነገሮች በማግለል ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ የምታሳልፈው ጊዜ ይኑርህ። «ጌታ ሆይ፣ በውስጤ ያለው ኃጢአት መሞቱን እርግጠኛ እስክሆን ድረስ ከሞትህ ጋር መተባበርን እፈልጋለሁ» በማለት ይህን እጅግ አስፈላጊ ውሳኔ እንድታደርግ እመክርሃለሁ። በኃጢአት ላይ የሞት ፍርድ እንዲደረግበት ጽኑ ውሳኔ አድርግ።

ለጳውሎስ ይህ ውሳኔ ገና ወደፊት የሚደርስበት ነገር አልነበረም፤ በዚህ ሕይወት እያለ የተረዳው ሥር ነቀል የሕይወት ልምምድ ነበረው። መንፈሳዊ ሕይወትህ ያለበትን ሁኔታ እንዲያሳይህ መንፈስ ቅዱስ ሕይወትህን እንዲመረምር ፈቃደኛ ነህ? በሕይወትህ ያሉ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ትግል የገጠሙ ነገሮችን እንዲያመለክትህ ትፈልጋለህ? ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ፊት ፈቃደኛነትህን ካሳስተካከልህ በቀር «ለኃጢአት እንደሞታችሁ ራሳችሁን ቍጠሩ» የሚለው ቃል በሕይወትህ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም (ሮሜ 6፣11)።

የእርሱ ሕይወት ሕይወትህ እስኪሆን ድረስ ከክርስቶስ ጋር ለመሰቀል ውሳኔ አድርገሃል? «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም፤ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል» (ገላ 2፣20)።

ቆራጥና የማያወላውል መለኮታዊ ሥራ

«ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውንም በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን» (ሮሚ ፮፣፭)

ከክርስቶስ ጋር መኖሣት፡፡ የኢየሱስን ሞት ለመለማመዱ ዋናው ማስረጃ እርሱን መምሰሉ ነው፡፡ ወደውስጤ የገባው የኢየሱስ መንፈስ በእግዚአብሔር ፊት ሕይወቴ እንዲስተካከል ያደርጋል፡፡ በትንሣኤው አማካይነት የእግዚአብሔርን ሕይወት ሰጥቶኛል፤ ስለዚህም ሕይወቴ የሚመሠረተው በዚህ ከእርሱ በተቀበልሁት ሕይወት ነው፡፡ አሁን የኢየሱስን ትንሣኤ ሕይወት አለማመዳለሁ፤ ይህም በምኖረው የቅድስና ሕይወት ይታያል፡፡

ከሐዋርያው ጳውሎስ ጽሑፎች መረዳት እንደምንችለው ከኢየሱስ ሞት ጋር ለመተባበር ውሳኔ ካደረግን በኋላ፤ የክርስቶስ ትንሣኤ ሕይወት ወደ ሁለንተናችን ይዘልቃል፡፡ በዚህ ሥጋችን የእግዚአብሔርን ልጅ ሕይወት ለመኖር ደግሞ ሁሉን የሚችል አምላክን መለኮታዊ ሥራ ይጠይቃል፡፡ ወደ ቤታችን እንደሚመጣ እንግዳ ለመንፈስ ቅዱስም አንዱን ክፍል ብቻ መስጠት ሳይሆን መላው እኛነታችንን ልንሰጠው ይገባል፡፡ አሮጌውን ሕይወቴን ለክርስቶስ ሞት ካስገዛሁ፤ መንፈስ ቅዱስ ሁሉ ነገሬን ይቈጣጠራል፤ ለሁሉም ነገሬ ጎላፊው እርሱ ይሆናል፡፡ የእኔ ድርሻ በብርሃን መመላለስና እርሱ ለገለጸልኝ ነገር መታዘዝ ብቻ ነው፡፡ ኃጢአትን በተመለከተ አንድ ጊዜ ይህን ታላቅ ውሳኔ ሳደርግ ለኃጢአት እንደሞትሁ መቍጠር እችላለሁ፤ ምክንያቱም የኢየሱስ ሕይወት ሕይወቴን የሚገዛው ያኔ ነው (ሮሚ ፮፣፲፩)፡፡ አንድ ዓይነት ሥጋዊ ሕይወት እንዳለ ሁሉ አንድ ዓይነት የቅድስና ሕይወት አለ፡፡ እርሱም የኢየሱስ ቅድስና ነው፡፡ የተሰጠኝም ይኸው የእርሱ ቅድስና ነው፡፡ እግዚአብሔር የልጁን ቅድስና በውስጤ አኑሮአል፤ ስለዚህም የአዲስ መንፈሳዊ ሥርዓት ተጠቃሚ ነኝ፡፡

የኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ሕይወታችንን መግዛት

«ሞትም ወደፊት እንዳይገዛው እናውቃለን፡፡ በሕይወት መኖርን ግን ለእግዚአብሔር ይኖራል፡፡ እንዲሁም እናንተ ደግሞ ለኃጢአት እንደሞታችሁ ለእግዚአብሔር ግን ሕያዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን ቍጠሩ፡፡» (ሮሜ 6፣9-11)

ከእርሱ ጋር ዘላለማዊ ሕይወትን መካፈል፡፡ የዘላለም ሕይወት ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰዎች የሚገልጸው ሕይወት ማለት ነው፡፡ ዳግም በተወለድሁበት ጊዜ በሥጋዊ ሕይወቴ የተገለጸውም ይኸው የዘላለም ሕይወት ነው፡፡ የዘላለም ሕይወት ከእግዚአብሔር የተለየ ሕይወት ሳይሆን የራሱ የእግዚአብሔር ሕይወት ነው፡፡ ኃጢአትን በተመለከተ ይህን የማያወላውል ቁርጥ ውሳኔ ስናደርግ በእግዚአብሔር ጸጋ አማካይነት የኢየሱስ ሕይወት ኃይል በሕይወታችን ይገለጻል፡፡

«መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ» (የሐዋ 1፣8)፡፡ ይህ ኃይል ራሱ መንፈስ ቅዱስ እንጂ ከእርሱ የተለየ ኃይል አይደለም፡፡ ከእርሱ ጋር ለመተባበር አንድ ጊዜ ውሳኔ ካደረግን ከመስቀሉ የተነሣ በኢየሱስ የነበረ ሕይወት የእኛም ይሆናል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ማስተካከል የሚያቅተን ኃጢአትን በተመለከተ የዚህ ዓይነት ውሳኔ ስላላደረግን ነው፡፡ እዚህ ውሳኔ ላይ ከደረስን ግን የእግዚአብሔር ሕይወት ሕይወታችንን ይቈጣጠራል፡፡ ኢየሱስ የመጣው «እስከ እግዚአብሔር ፍጹም ሙላት» እንድንደርስ ነበር (ኤፌ 3፣19)፡፡ የዘላለም ሕይወት ከጊዜ ጋር ግንኙነት የለውም፡፡ የዚህ ሕይወት ምንጩ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

ማንኛውም ፈቃደኛ የሆነ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ልጅን መለከታዊ ኃይል መለማመድ ይችላል፡፡ በራሳችን ጥረትና ብርታት የምንተማመን እስከሆንን ድረስ ግን የኢየሱስ ሕይወት በሕይወታችን ጐልቶ አይታይም፡፡ ፈቃደኞች ከሆንን፣ ቀስ በቀስ - ሆኖም በእርግጠኝነት ማንኛውም ነገራችንን ሰንጥቆ ማለፍ የሚችል የእግዚአብሔር ሕይወት ሕይወታችንን ይቈጣጠራል፡፡ በዚያን ጊዜ ሙሉ በሙሉ ኢየሱስ ሕይወታችንን ይገዛል፣ ሌሎችም ከእርሱ ጋር እንደ ነበርን ያውቃሉ፡፡

ሽክምህ ሲበረታ ምን እንደምታደርግ

«የከበደህን ነገር በእግዚአብሔር ላይ ጣል» (መዝ. 55፣22 ሰ.መ.ት)

ሸክም የሚገባንንና የማይገባንን የሸክም ዓይነት ማወቅ አለብን። የኃጢአትና የጥርጥር ሸክሞችን መሸከም የለብንም፤ ይሁን እንጂ አንዳንድ ሸክሞችን የሚጭንብን ራሱ እግዚአብሔር ስለሆነ ከእኛ ላይ አያነሣቸውም። እነዚህን ሸክሞች በእርሱ ላይ እንድንጥላቸው ነው የሚያሳስበን። «የከበደህን ነገር በእግዚአብሔር ላይ ጣል» የሚለንም እንዲህ ያለውን ሸክም ነው። እግዚአብሔርን እናገለግላለን፤ የእርሱን ሥራ እንሠራለን እያልን ከእርሱ ጋር ጥብቅ ግንኙነት ከሌለን ቦጎላፊነቱ ሸክም ስለሚከብደን ተሸናፊዎች እንሆናለን። እርሱ የሰጠንን ሸክም በእርሱ ላይ ከጣልን ግን ቦጎላፊነቱን ሸክም ከእኛ ይወስዳል፤ ይበልጥ እርሱን የማወቅ ግንዛቤ ይኖረናል፤ የመገኘቱም ኃይል ይሰማናል።

ብዙዎች በቅን ዓላማና ድፍረት ተነሣሥተው እግዚአብሔርን ማገልገል ይፈልጋሉ። ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ተገቢ ኅብረትና ግንኙነት ስለሌላቸው ግን አይሳካላቸውም። ሸክማቸውን በተመለከተ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ስለማያውቁ ታካችና ስልቹዎች ይሆናሉ። ይህንንም የሚመለከቱ ሁሉ «በመልካም ሁኔታ የተጀመረ ነገር በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ማለቁ ያሳዝናል» ይላሉ።

«የከበደህን ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ጣል።» እስካሁን ድረስ ሸክምህን በሙሉ በግልህ ተሸክመሃል፤ ከእንግዲህ ወዲህ ግን ሸክምህን በእርሱ ትከሻ ላይ መጣል አለብህ። «አለቅነትም በጫንቃው (በትከሻው) ላይ ይሆናል» (ኢሳ. 9፣6)። ከእርሱ የተቀበልከውን ማንኛውንም ሸክም በእግዚአብሔር ላይ ጣለው። ከሸክምህም ጋር ራስህን በእርሱ ፊት ጣል። ከእርሱ ጋር ካለህ ኅብረት የተነሣ ከትከሻህ ላይ ሸክሙ ሲነሣልህ ታያለህ። ይሁን እንጂ ራስህን ከሸክምህ መለየት የለብህም፤ ከሸክምህ ጋር ራስህንም ስጠው።

የማይሸነፍ ውስጣዊ ኃይል

«ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፣ ከእኔም ተማሩ» (ማቴ. 11፣29)

«ጌታ የሚወድደውን ይቀጣዋልና» ይላል ቃሉ (ዕብ. 12፣6)። እኛ ግን ምንኛ አጥረምራሚዎች ነን! ከእርሱ ጋር ትክክለኛ ኅብረትና ግንኙነት ወደምናደርግበት ስፍራ ጌታ ሲወስደን፣ «ጌታ ሆይ፣ ይህስ ይቅርብኝ፤ እንደሌሎች መኖር እፈልጋለሁ» በማለት ማጥረምረምና መነጫነጭ እንጀምራለን። ከእርሱ ጋር በአንድነት እንድንሸከመው የቀንበሩ ሌላኛው ጫፍ እኛ ላይ እንዲያርፍ ኢየሱስ ይፈልጋል። «ሸክሜ ቀሊል ነውና» የሚለንም ከዚህ የተነሣ ነው (ማቴ. 11፣30)። ታዲያ በዚህ ሁኔታ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ተባብረህ ይሆን? እንደዚያ ከሆነ አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር እጅ ቢከብድህ እንኳ ከማጥረምረም ይልቅ እግዚአብሔርን ታመሰግናለህ።

«ጉልበት ለሌለውም ብርታት ይጨምራል» (ኢሳ. 40፣29)። እግዚአብሔር መጥቶ ከስሜታዊነታችን ሊያላቅቀን በማጥረምረም ፈንታ የምስጋና ዜማን እናዜማለን። የእግዚአብሔርን ብርታት የምንለማመደው የኢየሱስን ቀንበር ስንሸከምና ከእርሱ ስንማር ነው።

«የእግዚአብሔር ደስታ ኃይላችሁ ነውና» (ነህ. 8፣10)። ቅዱሳን ደስታን የሚያገኙት ከየት ነው? ቀረብ ብለን በሚገባ የማናውቃቸው ከሆነ አንዳንድ ክርስቲያኖችን ምንም ዓይነት ሸክም የሌለባቸው ሊመስለን ይችላል። ሐቁን ለማየት ግን ዓይናችንን የጋረደው መጋረጃ መገለጥ አለበት። ሰላም፣ ደስታና ብርሃን በሕይወታቸው መኖሩ ራሱ የራሳቸው ሸክም እንዳላቸው ማስረጃ ነው። እግዚአብሔር በእኛ ላይ ያኖረው ሸክም ሲጫነን የሕይወታችን ወይን ፍሬ ይጨመቅና ወይን ጠጅ ይወጣዋል፤ ብዙዎቻችን ግን የምናየው ጫናውን ሳይሆን ወይኑን ነው። በምድርም ሆነ በገሃነም ያሉ ኃይላት በሰው መንፈስ ውስጥ የሚኖረውን የእግዚአብሔር መንፈስ ማሸነፍ አይችሉም፤ የማይሸነፍ ውስጣዊ ኃይል ሊኖረን የሚችለውም ከዚህ የተነሣ ነው።

እንዲህ ያለው ፍሬ ከሕይወትህ እንዳይገኝ እንቅፋት የሚሆንብህን ነገር ያለ ርኅራኄ ቆርጠህ ጣለው። የእግዚአብሔርን ኃይል የተቀበለ ክርስቲያን ደካማ ሆኖ መገኘቱ ራሱ በደል ነው።

ያለማስተዋል የሚያስከትለው ችግር

«በኮረብታ ላይ የነበሩትን መስገጃዎች ግን ከስስራሌል ስላሌቀም፣ ደሙን እንጂ የስሳ ዯብ በዘመኑ ሁለ ፍጹም ነበር» (2ዜና 15፣17)

በሚታየውና ውጫዊ በሆነው የሕይወት ገጽታው አሳ ሙሉ በሙሉ አልታዘዘም። በጣም አስፈላጊ በሆነው ጉዳይ ታዛዥነቱን ቢያሳይም መታዘዙ የተሟላ አልነበረም። መታዘዝን በተመለከተ «እንዲህ ያለው ጉዳይ ይህን ያህል አስፈላጊ አይደለም» በማለት መዘናጋት የለብንም። ምክንያቱም ለእኛ አስፈላጊ ያልሆነ ነገር ለእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። አንድ ክርስቲያን ቀላል ወይም የማይረባ ነው ብሎ የሚተወው ነገር መኖር የለበትም። በጣም ጥቃቅን ስለሆኑ ነገሮች እንኳ ቢሆን እግዚአብሔር እንዳያስተምረን መሰናክል የምንሆነው እስከ መቼ ነው? እግዚአብሔር ግን በትዕግሥት ዘወትር ሊያስተምረን ዝግጁ ነው። «በኮረብታ ላይ» ያሉትን መስገጃዎች እስካላስወገድን ድረስ ሙሉ በሙሉ ታዛዦች አይደለንም፤ ስለዚህም ትክክል ነኝ በማለት መኩራራት የለብንም። የምትጠራጠርበት ነገር በሕይወትህ መኖሩን እያወቅህ ልብህ በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም እንደሆነ ታስባለህን? በአንድ ነገር ልብህ ከተጠራጠረ ምንም ይሁን ምን ወዲያውኑ ልትተወው ይገባል። በሕይወትህ በሚሆነው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ጥቂት ነው ወይም የማይረባ ነው ብሎ የሚያልፈው ነገር እንደሌለ ማወቅ አለብህ።

በቸልታ የምታልፈው በዓይን የሚታይ አካላዊ ወይም አእምሮአዊ ችግር አለን? እንደዚያ ከሆነ በጣም አስፈላጊ ናቸው በምትላቸው ነገሮች ትክክል ብትሆንም፣ አንዳንድ ትኮረት ያልሰጠሃቸው ነገሮች አሉ ማለት ነው። ዛሬ እረፍት ላድርግ ብሎ ለአንድ ቀን እንኳ ልብህ መምታቱን እንደማያቆም ሁሉ፣ አንተም ከመንፈሳዊ ነገር መዘናጋት አይኖርብህም። ከግብረ ገባዊ ነገሮች አስከተዘናጋህ ድረስ ግብረ ገባዊ አይደለህም፤ ከመንፈሳዊ ነገር አስከተዘናጋህ ድረስ ደግሞ መንፈሳዊ አይደለህም። እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ የራሱ ሊያደርግህ ይፈልጋል፤ አንተም እርሱ ለሚፈልገው ነገር ትኮረት መስጠት አለብህ። ይህን ማድረግ ረጅም ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ይሁን እንጂ ብዙዎቻችን በአጭር ጊዜ ከአንዱ የተራራ ልምምድ ወደ ሌላው የተራራ ልምምድ መሸጋገር እንፈልጋለን።

ከተራራ ሕይወት መውረድ ትችላለህን?

«ብርሃን ሳላችሁ በብርሃኑ ስሙኑ» (ዮሐ. 12፣36)

ሰዓንኛችንም ብንሆን አንዳንድ ደስ የሚሉ ወቅቶችን አሳልፈናል፤ ስለዚህም «ሁልጊዜ እንዲህ ቢሆንልን የት በደረስን!» እንላለን። ሆኖም ነገሮች ሁልጊዜ እንደዚያ አይሆኑም። እነዚያ ወቅቶች ለሌላ ጊዜ የሚሆነን መገለጥ የምናገኝባቸው ወቅቶች ናቸው። ብዙዎቻችን ግን ደስ ለሚያሰኝ የተራራ ዓይነት ሕይወት እንጂ በየዕለቱ ለሚገጥሙን የሕይወት ውጣ ውረዶች የተዘጋጀን አይደለንም። ሆኖም በተራራው ልምምዳችን በተረዳነው እውነት መሠረት የዕለት ተዕለት ሕይወታችንንም መኖር ይገባናል።

ደስ በሚያሰኝ ወቅት ወይም በተራራው ሕይወት ልምምድህ የተረዳኸውን በፍጹም መዘንጋት የለብህም። «አቤት ያ ጊዜ እንዴት ደስ የሚል ነበር!» እያልክ በትዝታ መኖር የለብህም። በተረዳኸው መሠረት እርምጃ ውሰድ። ለምሳሌ ያህል በአንድ የጸሎት ስብሰባ ላይ እያለህ እግዚአብሔር አንድ ነገር ቢያመለክትህ ቆይ ነገ አትበል፣ ወዲያውኑ አንድ ነገር ማድረግ አለብህ። ለስንፍና ወይም ለታካችነት በፍጹም ስፍራ አትስጠው። ስላለፈው የተራራ ሕይወት ልምምድ እያሰላሰልህ መኖር ወይም ደግሞ እንዴት ወደዚያ የተራራ ሕይወት እንደምትመለስ እያውጠነጠንህ መኖር ስንፍና ነው። ደስ በሚል የተራራ ልምምድ እንደኖርን ሁሉ፣ ደስ በማያሰኙ ቀኖችም መኖር አለብን።

እንቅፋት ስላጋጠመህ ወይም በአንዳንድ ነገሮች ግራ ስለተጋባህ አንድን ነገር አትተው። ወደ ኋላ እንዳትመለስ የመሳህበትን ድልድይ አፍርሰው፣ በገዛ ፈቃደኝነትህ ለእግዚአብሔር በተሰጠህበት ነገር ጸንተህ ቁም እንጂ በፍጹም ተስፋ አትቊረጥ። በተራራው ላይ ባገኘኸው ብርሃን መሠረት ውሳኔ አድርግ እንጂ በውሳኔህ አታወላውል፣ ወይም በየጊዜው ውሳኔዎችህን አትለውጥ።

ሁሉን መተው ወይስ ምንም አለመተው?

«ስምዓን ጴጥሮስ ጌታ መሆኑን በሰማ ጊዜ ዕራቁቱን ነበረና ልብሱን ታጥቆ ወደ ባሕር ራሱን ጣለ» (ዮሐ. 21፣7)

ነገሮችን እርግፍ አድርገህ እንድትተው ያደረገህ ውጣ ወረድ በሕይወትህ ተፈጽሞ ያውቃልን? ውጣ ውረዱ የተፈጸመው በፈቃድህ ውስጥ ነበር። በውጫዊ ሁኔታ ብዙ ጊዜ ወደዚህ ውሳኔ መጥተህ ነበር፤ ሆኖም ይህን ያህል የጎላ ለውጥ በሕይወትህ አላመጣም። ለዘለቄታው ነገሮችን እንድትተው የሚያደርግ ወይም ራስን ሙሉ በሙሉ መስጠት የሚከናወነው አንተ ውስጥ እንጂ በምትተዋቸው ውጫዊ ነገሮች አይደለም። ውጫዊ ነገሮችን ብቻ መተውህ የሚያመለክተው ምናልባት ሙሉ በሙሉ የነገሮች እስረኛ ወይም ባርያ መሆንህን ሊሆን ይችላል።

ሆን ብለህና ፈቅደህ ፈቃድህን ለኢየሱስ ክርስቶስ አስገዝተህ ይሆን? ይህ ሁኔታ ፈቃድህን እንጂ ስሜትህን የሚመለከት አይደለም፤ ምናልባት ደስ ደስ የሚል ዓይነት ስሜት ቢኖርህ እንኳ ያ ማለት በልብህ ውስጥ ያደረግኸው ውሳኔ ውጤት እንጂ ሌላ ምንም ማለት አይደለም። ትኩረትህ ስሜትህ ላይ ከሆነ ግን እንደዚህ ዓይነት ውሳኔ ማድረግ አትችልም። እግዚአብሔር ባመለከተህ ነገር ቆራጥ እርምጃ ውሰድ እንጂ ከእርሱ ጋር ለመደራደር አትሞክር።

በማዕበል ውስጥ ሆኖ ኢየሱስ ክርስቶስ ተናግሮህ፣ ከሆነ፣ ትኩረትህ ሙሉ በሙሉ እርሱ ላይ ይሁን እንጂ የራስህን ስሜት ማድመጥ የለብህም።

ዝግጁነት

«እግዚአብሔር በጠራው ጊዜ እነሆኝ አለ» (ዘዳ. 3፣4)

እግዚአብሔር ሲናገረን በጭጋግ ውስጥ ያለ ሰው ዓይነት ስለምንሆን ብዙዎቻችን ምንም መልስ አንሰጥም። ሙሴ ለእግዚአብሔር የሰጠው መልስ የት እንዳለና ዝግጁ መሆኑን የሚያመለክት ነው። ዝግጁነት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ማድረግና የት አገልግሎ ማወቅ ነው። ብዙ ጊዜ ግን ለእግዚአብሔር የምንነግረው የት መሄድ እንደምንፈልግ ነው። ጥሪ ሲመጣ ሽልማቱን የሚቀበለው ለእግዚአብሔርና ለሥራው የተዘጋጀ ሰው ብቻ ነው። ብዙ ጊዜ አንድ የተለየ ዕድል ወይም ስሜታችንን የሚያነቃቃ ነገር እስኪገጥመን ድረስ እንጠብቃለን፤ የጠበቅነው ሲመጣም «እነሆኝ፣ እዚህ ነኝ» እንላለን። ትልልቅ ለሚመስሉን እንጂ ለትንንሾቹና ታዋቂነትን ለማያስገኙልን ነገሮች ዝግጁ አይደለንም።

ለእግዚአብሔር ዝግጁ መሆን ማለት ግን ለትንሹም ሆነ ለትልቁ ሥራ ምንጊዜም ታጥቆ መነሣት ማለት ነው። የራሳችን ምርጫ ሳይታከልበት ለማንኛውም የእግዚአብሔር እቅድ ዝግጁ መሆን ማለት ነው፤ የሥራው ትልቅ መሆን ወይም አለመሆን ምንም ልዩነት አያመጣም። አንድ የሚደረግ ነገር ሲኖር ጌታችን የአባቱን ድምፅ እንደ ሰማ ሁሉ እኛም የእግዚአብሔርን ድምፅ እንሰማለን፤ ለእርሱ ካለን ፍቅር የተነሣም ፍጹም ዝግጁዎች እንሆናለን። እግዚአብሔር አብ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እንደ ሠራ ሁሉ እርሱም ከእኛ ጋር መሥራት ይፈልጋል። እኛ ከእርሱ ጋር ያለን ግንኙነት እርሱ ከአባቱ ጋር ያለው ዓይነት ግንኙነት ስለሆነ አስደሳችም ይሁን ደስ የማያሰኝንን ሥራ ሊሰጠን ይችላል። «እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ» (ዮሐ. 17፣22)።

እግዚአብሔር ባሳሰብከውና ባልጠበቅኸው ሁኔታ ሊገናኝህ ስለሚችል ተዘጋጅ። የተዘጋጀ ሰው ደግሞ እንደ አዲስ መዘጋጀት አያስፈልገውም፤ ምክንያቱም ቀድሞውኑ ተዘጋጅቶአል። የእግዚአብሔር ጥሪ ሲመጣልን ለመዘጋጀት ስለምናባክነው ጊዜ አስብ። የተቃጠለው ቍጥቋጦ የተዘጋጀ ሰውን የከበቡት ነገሮች ምሳሌ ነው፤ የከበቡንን ነገሮች የሚያቃጥላቸው የራሱ የእግዚአብሔር መገኘት የሚፈጥረው እሳት ነው።

ጥቃቅን በሚመስልህ ፈተና እንዳትወድቅ ተጠንቀቅ

«ሊዮስብም ስቢሴሙምን ስህተከተሰም ነበር እንጂ ስዶንያስን ተከትሱ ነበር»
(1ነገ. 2፣28)

ኢብደኛውንና የሕዝብን ልብ የማረከውን አቤሴሎምን ባለመከተል ለዳዊት ታማኝነቱን ያረጋገጠው ኢዮአብ፣ በሕይወት ዘመኑ የገጠመውን ታላቅ ፈተና አልፎ ነበር። ይሁን እንጂ ወደ ሕይወቱ ማለቂያ አካባቢ ደካማውንና ፈሪውን አዶንያስን ለመከተል ፈቱን መልሶአል። አንድ ሰው ፈቱን ወደኋላ ሲያዞር በዚያው ወቅት ወደኋላ ለመመለስ እንደሚፈተን ምንጊዜም ቢሆን ማስታወስ አለብን። (1ቆሮ. 10፣11-13) ትልልቅና አስቸጋሪ ፈተናዎችን አልፈህ ይሆናል፤ በጣም አነስተኛና ዝቅተኛ መስሎ በሚታይህ ፈተና እንዳትወድቅ ደግሞ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብሃል። ባለፈው ጊዜ በድል ያለፍከው ፈተና በአሁኑ ጊዜ ለመሰናክልና ለመውደቅ ምክንያት ሊሆን አይችልም በማለት አታስብ።

«ባለፈው ጊዜ ያንን የመሰለ ትልቅ ፈተና አልፌአለሁ፤ ስለዚህም ትንንሽ ዓለማዊ ፈተናዎች ሊያሸንፉኝ አይችሉም» በማለት እናስባለን። ፈተናው በየት በኩል እንደሚመጣ በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም፤ እንዲያውም በጣም አደገኞቹ ጥቃቅን የሚመስሉን ነገሮች ናቸው። ጥቃቅን መስለው በሚታዩን ፈተናዎች ብቅ ብቅ ማለት የሚጀምሩት ከትልቅ መንፈሳዊ ድል በኋላ መሆኑን አትዘንጋ። ይህን ያህል ከባድ ወይም አዳጋች ሳይሆኑ ይችላሉ፤ ያም ሆኖ ግን አደገኞች ናቸው። ጥንቃቄ ካላደረግህ እነዚያ ጥቃቅን የሚመስሉ ነገሮች ጠልፈው ይጥሉሃል። በትልልቅ ፈተናዎች መካከል ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆንህን አስመስክረህ ይሆናል፤ አሁን መጠንቀቅ ያለብህ ደካማ መስለው የሚታዩ ፈተናዎችን ነው።ያለፈውን ዘመን በንቃት አስታውስ፤ ማንኛውንም ፈተና አቅልለህ አትመልከት። ልቅ የወጣ ብርታት እጥፍ ደካማነት ነው፤ ምክንያቱም በጣም ጥቃቅን የሚመስሉህ ነገሮች ኃይልና ብርታትህን የሚያሟጥጡት በዚያን ጊዜ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምንመለከታቸው ታላላቅ ሰዎች ተሰናክለው የወደቁት በብርቱ ጉናቸው እንጂ በደካማ ጉናቸው አልነበረም።

ጴጥሮስ «በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠበቃችሁ» ይላል፤ አስተማማኙም ይኸው ነው (1ጴጥ. 1፣5)።

በሐሰት እግዚአብሔርን መውቀስ

«እግዚአብሔር ስለጠፋው የተሰፋ ቃል ዙሪ ስዎን ማለት በእርሱ ነውና» (2ቆሮ. 1፣20)

በማቴዎስ 25፣14-30 ስለመክሊቶቹ የተሰጠው ምሳሌ አቅማችንን አሳንሰን እንዳንመለከት የሚያሳስብ ማስጠንቀቂያ ነው። መክሊት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን እንጂ ተፈጥሮአዊ ስጦታችንን ወይም ችሎታችንን የሚወክል አይደለም። መንፈሳዊ አቅማችንን በትምህርት ደረጃችን ወይም በአእምሮ ብስለታችን ልንለካው አይገባም፤ መንፈሳዊ አቅማችን የሚለካው እግዚአብሔር በሰጠን ተስፋ መሠረት ነው። እግዚአብሔር ብዙ ሰጥቶን እያለ እኛ ግን የተቀበልነው ጥቂቱን ከሆነ እንደዚያ« የሰጠኸኝ ጥቂት ነው፤ አንተ ግን ብዙ ትጠብቅብኛለህ፤ በሰጠኸኝ ጎላፊነት ታማኝ ልሆን ያልቻልኩትም በዚህ ምክንያት ነው» በማለት በሐሰት ጌታውን እንደ ከሰሰ ባርያ ነው የምንሆነው። ሁሉን ቻይ የእግዚአብሔር መንፈስን በተመለከተ «ከአቅሜ በላይ ነው» የምትለው ምንም ነገር ሊኖር አይገባም። የተፈጥሮ ችሎታህ ውሱንነት እንቅፋት አንዲሆን አትፍቀድ፤ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለህ ከሆነ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በሕይወትህ እንዲታይ እግዚአብሔር ይጠብቅብሃል።

ያ ባርያ ራሱን ትክክለኛ ለማድረግ በማሰብ ጌታውን በደለኛ አድርጎአል። ከሰጠው ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው «የሰጠኸኝና ከእኔ የምትጠብቀው በፍጹም አይመጣጠንም» ነበር ያለው። «አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል» የሚል የተሰፋ ቃል ተሰጥቶናል፤ አንተ ግን የምትጨነቅ ከሆነ እግዚአብሔርን በሐሰት እየከሰስከው እንደሆነ አስተውለህ ይሆን? (ማቴ. 6፣33)። «እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ያደረግኸኝ እኔን ለችግር ለማጋለጥ ነው» በማለቱ ያ ባርያ ያለበትን ጭንቀት ነበር ያሳየው። በሥጋዊ ሕይወቱ ሰነፍ የሆነ ሰው «ሁኔታዎች አልተመቻቹልኝም» ወይም «የአርባ ቀን ዕድሌ ጠምሞብኛል» በማለት ያማርራል፤ መንፈሳዊ ነገርን በተመለከተ ሰነፍ የሆነ ክርስቲያን ደግሞ እንዲሁ በእግዚአብሔር ላይ ያጉረመርማል። ምንጊዜም ቢሆን ሰነፎች እንደ ምክንያት የሚያቀርቡት ሌሌችን ነው።

የመንፈሳዊ አቅማችን ወይም የመንፈሳዊ ብቃታችን መሠረቱ የእግዚአብሔር ተስፋ መሆኑን በፍጹም መዘንጋት የለብንም። የገባውን ተስፋ ለመፈጸም እግዚአብሔር አቅም ይኖረዋልን? መልሱን የሚወስነው መንፈስ ቅዱስን መቀበል አለመቀበላችን ነው።

ጌታን ማሳዘን

«ሲየሱስም ስሰው ስንተ ፌልጶስ ደህን ያህሰ ዘመን ከስናንተ ጋር ስኖር ስታውቂኝምን?» (ዮሐ. 14፣9)

ገሮች አለመሆናችን ጌታን በጣም ሳያስደንቀው እንደማይቀር አስባለሁ። አንድን ነገር ለመረዳት ወይም ለመቀበል ዘገምተኞች የምንሆነው ገሮች ስላይደለን ነው፤ ገሮች ብንሆን ኖሮ ያለምንም ማወላሰብ ነገሮችን እንለይ ነበር፣ በቀላሉም እንቀበል ነበር። ፊልጶስ ወደፊት ይገለጻል ብሎ የሚያስበውን የእግዚአብሔርን ምሥጢር እየተጠባበቀ ነበር፤ ሆኖም ከረጅም ጊዜ በፊት በሚያውቀው በኢየሱስ በኩል ይሆናል ብሎ አሳሰበም ነበር። የእግዚአብሔር ምሥጢር በጣም አስደናቂ በሆነ ሁኔታ ወደፊት ይገለጻል ብለን እናስባለን፤ የእግዚአብሔር ምሥጢር ግን አሁን ተገልጾአል። ያለምንም ማመንታት ለኢየሱስ ለመታዘዝ ፈቃደኞች ነን፤ ይሁን እንጂ «እግዚአብሔርን አሳየን»በማለት በምናቀርበው ጥያቄ ጌታን እናሳዝነዋለን (14፣8)። ለጥያቄያችን የሚሰጠን መልስ «እርሱን የትም ቦታ አታገኙትም፤ ምክንያቱም እርሱ ሁልጊዜ እዚህ ነው» የሚል ይሆናል። እግዚአብሔር ለልጆቹ ራሱን ይገልጣል ብለን እንጠብቃለን፣ እግዚአብሔር ግን በልጆቹ ራሱን ገልጾአል። ይህን ማስረጃ ሌሎች ሲያስተውሉ የእግዚአብሔር ልጆች ግን አላስተዋሉም። እግዚአብሔር በውስጣችን እየሠራ ያለውን ነገር ለማወቅ እንፈልጋለን፤ ሙሉ በሙሉ ልናውቅና ከእርሱ የምንጠብቀውን ነገር በሚመለከት ምክንያታዊ ወይም ሚዛናዊ ለመሆን አንችልም፤ ብዙ ጊዜ ልባችንን ጌታ ላይ ሳይሆን ልምምዳችን ላይ እናደርጋለን። በዚህም ወደበለጠ መረዳት እንዳናድግ መንገድ እንዘጋለን። ይህም ደግሞ ጌታን ያሳዝነዋል። አንዳንድ የምናቀርባቸው ጥያቄዎች በቅርቡ ጌታን ከሚያውቁ ሰዎች እንኳ የሚሰነዘሩ ጥያቄዎች አይደሉም።

«ልባችሁ አይታወክ» ብሎናል (14፣1,27)። ታዲያ በትንሽ በትልቁ በመታወካችን ጌታን እናሳዝነው ይሆን? በኢየሱስና በባሕርያቱ የማምን ከሆነ በማምነው መሠረት እየኖርሁ ነው? በተለያዩ ነገሮች እታወካለሁ? ተገቢ ያልሆኑና ሚዛናዊነት የሌላቸው ጥያቄዎችስ አለምሮዬን ገዝተውታል? ከእርሱ የሆነውን ነገር መቀበል እንድችል ከእርሱ ጋር ተገቢ ግንኙነትና ኅብረት ሊኖረኝ ይገባል። እግዚአብሔር የሚመራን ገና ወደፊት አይደለም፤ እግዚአብሔር አሁን እየመራን ነው። እርሱ የሚመራን እዚህና አሁን እንደሆነ አስተውል፤ ነጻነትን ከእርሱ የምንቀበለውም እዚህና አሁን ነው።

በፍጹም የማይደበዝዝ ብርሃን

«በመጋረጃ በሚደክደን ፊት የጌታን ክብር እያየንጨለሞን...» (2ቆሮ. 3፣18)

ከንድ የእግዚአብሔር አገልጋይ ብቸኝነት እስከማይሰማው ድረስ ብቻውን መሆንን መልመድ ይኖርበታል። አንዳንድ ጊዜ በክርስትና ሕይወታችን ተስፋ መቁረጥ ይሰማናል፡ እንደ ብርሃን እንመለከታቸው የነበሩ ሰዎችም ይደበዝዙብናል፡ አብረውን የነበሩም ጥለውን ዘወር ይላሉ። ብቻችን መሆናችን እስከማይታወቀን ድረስ እንዲህ ዓይነቱን ሁኔታ መልመድ ይኖርብናል። በአንድ ወቅት ጳውሎስ ሲናገር «አንድ ስንኳ አልደረሰልኝም፣ ሁሉም ተዉኝ እንጂ.... ዳሩ ግን ጌታ በእኔ አጠገብ ቆሞ አበረታኝ» ብሏል (2ጢሞ. 4፣16-17)። እምነታችንን ምንጊዜም አስተማማኝ በሆነ ብርሃን እንጂ እያዩር በማይደበዝዝ ብርሃን ላይ ማድረግ የለብንም። መሄድ ስላለባቸው የምንተማመንባቸው ሰዎች ጥለውን ሲሄዱ ፊታችንን ወደ እግዚአብሔር ብቻ እናቀናለን፡ በዚያን ጊዜ የእነዚያ ሰዎች መሄድ ለበለጠ ጥቅም እንደሆነ እንረዳለን።

ሕይወትህን ሆነ የምትከተለውን አስተምህሮ በተመለከተ የእግዚአብሔርን ፊት ብቻ ለመፈለግ ከምታደርገው ቆራጥ ውሳኔ ምንም ነገር አያዘናጋህ። ከመስበክህ በፊት በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን ፊት ፈልግ፡ በዚያን ጊዜ ስብከትህ የእርሱን ክብር የሚያሳይ ይሆናል። አንድ ክርስቲያን አገልጋይ ዘወትር የእግዚአብሔርን ፊት ይፈልጋል፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ ለሌሎች ይናገራል። ዘወትር በእግዚአብሔር ክብር ውስጥ ስለሚኖር በዚያ ክብር ውስጥ መኖሩን እንኳ አያውቀውም። ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገር በነበረበት ጊዜ ፊቱ ማብራቱን አላወቀውም ነበር (ዘጸ. 34፣29)። የአንድ አገልጋይ ሕይወት መሳካት ምሥጢሩ ዘወትር ከእግዚአብሔር ጋር መስማማቱ ነው።

ሥራውን እያመለክህ ይሆን?

«ክርስቶስ ጋረ ስብረን የሥንሠራ ነንና...» (1ቆሮ. 3፣9)

ትኮረትህን ከእግዚአብሔር ላይ አንሥተህ የእግዚአብሔር ሥራ ላይ እንዳታደርግ ተጠንቀቅ። ብዙ አገልጋዮች አገልግሎታቸውን ያመልኩታል። የአገልጋዮች ትልቁ ትኮረት በእግዚአብሔር ላይ ብቻ መሆን አለበት። እንዲህም ከሆነ እግዚአብሔር ከሚሰጠው ነጻነት የተነሣ አገልጋዩ ከማንኛውም ውሱንነት ነጻ ይሆናል ማለት ነው። ሙሉ ትኮረቱን በእግዚአብሔር ላይ የማያደርግ አገልጋይ ከሚገባ በላይ በሥራው ጫና ይጐዳል፡ የራሱ ውሱንነት ባርያ ስለሚሆን የአካል፣ የአእምሮና የመንፈስ ነጻነት አይኖረውም፣ የዚህ ዓይነት ሕይወት ደስተኛ ሕይወት አይደለም። አካልና ልቡ ውጥረት ላይ ስለሚሆን የእግዚአብሔርን ባርኮት አይለማመድም።

በሌላ በኩል ደግሞ ሙሉ ትኮረታችንን በእግዚአብሔር ላይ ካደረግን ደካማነታችንና ውሱንነታችን በእግዚአብሔር ቍጥጥር ሥር ይሆናል። የሥራው ጎላፊዎች እግዚአብሔር እንጂ እኛ አንሆንም። የእኛ ድርሻ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ማጥበቅና ከእርሱ ጋር ጎበረት እንዳይኖረን መሰናክል የሚሆኑ ነገሮችን ማስወገድ ነው። ቅድስናን ስንለማመድ የምናገኘው ነጻነት ወደ ኋላ ከሚስበንና ወደ ታች ከሚጐትተን ሸክም ነጻ ያደርገናል። ያ ነጻነት በሙሉ ፈቃደኛነት ከእርሱ ጋር አብረን እንድንሠራ የሚያስችል ነጻነት መሆኑን መዘንጋት የለብንም።

ሁኔታዎችን ሁሉ የሚመራና የሚያቀነባብረው እግዚአብሔር ራሱ ስለሆነ የት ወይም ወዴት እንዲያሰማራን የመምረጥ ወይም የመወሰን መብት የለንም። እርሱ ለሰጠን ሥራ ሁለንተናችንን ማሳተፍ አለብን። በዚያን ጊዜ «እጅህ ለማድረግ የምታገኘውን ሁሉ እንደ ኃይልህ አድርግ» (መክ. 9፣10)።

በመንፈሳዊ ስኬትህ አትመካ

«ነገር ግን መፍቼስት ስሰተገዙላችሁ በዚህ ደስ ስደበሳችሁ» (ሱቃ. 10፣20)

ብዙ ጊዜ አገልጋዮች መጠንቀቅ ያለባቸው ከዓለማዊነት ወይም ከኃጢአት አይደለም። አገልጋዮች መጠንቀቅ ያለባቸው መንፈሳዊ ስኬትን በዚህ ዓለም መለኪያ መሠረት እንዳይመዝኑ ነው። ምንጊዜም ቢሆን ዓላማችን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት ብቻ ይሁን። አገልግሎት ስለተሳካላቸውና ስለተከናወነላቸው ብቻ መደሰት እንደሌለባቸው ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን አስጠንቅቆአል፤ እኛ ግን ይህን ስናደርግ ነው የምንስተዋለው። ለአገልግሎት ያለን አመለካከት የትርፍና ኪሳራ ስሌት ዓይነት ነው፤ ምን ያህል ሰዎች ጌታን እንደተቀበሉ፣ ምን ያህሉቹ ቅድስናን እንደተለማመዱ እንቆጥርና ሁሉም ነገር ያለቀለት ይመስለናል። ይሁን እንጂ፣ የእግዚአብሔር ጸጋ መሠረቱን በሣለበት ስፍራ ሁሉ የእኛ ሥራ ገና መጀመሩን መረዳት አለብን። የእኛ ድርሻ ሰዎችን ደቀ መዛሙርት ማድረግ እንጂ ሰዎችን ማዳን አይደለም። ደኅንነትና ቅድስና የእግዚአብሔር ጸጋ ውጤቶች ናቸው፤ ከእኛ የሚጠበቀው ሙሉ በሙሉ ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር ማስገዛት ይችሉ ዘንድ ሰዎችን ደቀ መዛሙርት ማድረግ ነው። ደኅንነት እንደሚያስፈልጋቸው ከተገነዘቡ መቶ ሰዎች ይልቅ አንድ ሰው ሙሉ በሙሉ ሕይወቱን ለእርሱ ማስገዛቱ በእግዚአብሔር ፊት የበለጠ ዋጋ አለው። እንደ መንፈሳዊነታችን መንፈሳውያን ሰዎችን ማፍራት ይኖርብናል፤ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ለመሆናችን ምስክሮቹም እነዚያ ሰዎች ናቸው። በጸጋው አማካይነት እግዚአብሔር ለሌሎች ምሳሌ እንድንሆን ያስችለናል፤ ሌሎችም ምሳሌነት ያለው ሕይወት እንዲኖሩ ማድረግም ይጠበቅብናል።

«ሕይወታችሁ በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአል» (ቈላ. 3፣3)። ሕይወቱን በሙሉ በክርስቶስ ውስጥ ያሳደረ አገልጋይ ምሳሌ የሚሆን ሕያው ደቀ መዝሙር ሳይሆን ሌሎችን የሚያስጨንቅና የሚያስመርር አምባገነን ይሆናል። ብዙዎቻችን አስተሳሰብና አመለካከታችንን ሌሎች አሜን ብለው እንዲቀበሉ ማድረግ የምንሞክር አምባ ገነኖች ነን። ጌታችን ስለደቀ መዝሙርነት በተናገረበት ስፍራ ሁሉ «ማንም ቢወድ» አለ እንጂ «ወደዳችሁም ጠላችሁም ደቀ መዛሙርቴ መሆን አለባችሁ» አላለም። ደቀ መዝሙርነት የምርጫ ጉዳይ ነው።

ሁልጊዜ ዝግጁ መሆን

«... ጊዜው ቢመችም ባይመችም ዝግጁ ሁን» (2ጢሞ. 4፣2 ሕ.መ.ት)

ብዙዎቻችን «ቢመችም ባይመችም» የሚለውንና «ዝግጁ ሁን» የሚሉትን ቃላት ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ መረዳት ይከብደናል። በመሠረቱ «ቢመችም ባይመችም» የሚለው ቃል ጊዜውን ሳይሆን የሚመለከተው እኛን ነው። «ቢመችም ባይመችም በማንኛውም ጊዜ ዝግጁ ሁን ቃሉን ስበክ» ይላል። በሌላ አነጋገር ቢሰማንም ባይሰማንም፣ ቢመስለንም ባይመስለንም፣ በማንኛውም ጊዜ ዝግጁ መሆን አለብን ማለቱ ነው። ሲመቸን ወይም ሲሰማን እንሠራለን ብንል ኖሮ ብዙዎቻችን ምንም ነገር አንሠራም ነበር። አንዳንድ ሰዎች አንድ ዓይነት መለኮታዊ ኃይል እስኪያነሣሣቸው ድረስ ስለሚጠብቁ ምንም መሥራት አይፈልጉም፤ እነዚህ ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ደካሞችና ልፍስፍሶች ናቸው። ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ኅብረት ያለን ለመሆኑ አንዱ ማስረጃ፣ ቢሰማንም ባይሰማንም የሚቻለንን ሁሉ ማድረጋችን ነው።

የክርስቲያን አገልጋዮች ዋናው ችግር የእግዚአብሔር መንፈስ እስኪያነሣሣቸው ድረስ መጠበቃቸው ነው። አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ ሊያነሣሣን፣ አስፈላጊውንም ምሪት ሊሰጠን ይችላል፤ ስለሆነም ሁልጊዜ እንደዚያ ይሆናል ብለን የመጠበቅ ዝንባሌ ይኖረናል። እንደዚያ ያለው ጊዜ የእግዚአብሔር ስጦታ ስለሆነ እኛ በፈለግነው ጊዜ የምንፈጥረው አይደለም። የተለየ ጊዜን ወይም ምሪትን የምንጠብቅ ከሆነ ለእግዚአብሔር የማንመች አገልጋዮች እንሆንበታለን። የእግዚአብሔር መንፈስ ልዩ በሆነ ሁኔታ ልባችንን ካላነሣሣ በቀር ምንም ነገር ማድረግ አንፈልግም። ምቹ ጊዜ እስኪመጣ ድረስ የምንጠብቅ ከሆነ፣ ያንን ምቹ ጊዜ ጣያት አድርገነዋል ማለት ነው፤ በእግዚአብሔር መታመናችን ቀርቶ እምነታችን በዚያ ምቹ ጊዜ ላይ ይሆናል። እግዚአብሔር ባስቀመጠን በማንኛውም ስፍራ ታዛዥ ካልሆንን በቀር ከእርሱ ጋር የነበረን ትክክለኛ ጊዜ አይታደስልንም፣ የምንጠብቀው ምቹ ጊዜ በፍጹም አይመጣም።

ወደ ከፍታ መውጣት

«የምትወደውን ስንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ እኔ በምነግርህ በሰንድ ተራራ ላይ ሠዋሥዋት ስድርገህ ሠዋው» (ዘፍ. 22፣2)

የአንድ ሰው ጠባይ የእግዚአብሔር ፈቃድ በምን ዓይነት መልክ እንደሚተረጕመው ይመስናል (መዝ. 18፣25-26)። ልጁን እንዲሠዋ እግዚአብሔር አብርሃምን ባዘዘው ጊዜ ከባሕሳዊ እምነቱ የሚላቀቀው በዚህ በቀረበለት አስቸጋሪ ፈተና አማካይነት እንደሆነ ነበር የተረዳው። እግዚአብሔርም ቢሆን የአብርሃምን እምነት እርሱ እንደሚፈልገው ለማድረግ ሌላ መንገድ አልነበረውም። በቅንነት ለእግዚአብሔር ስንታዘዝ ስለ እርሱ ካለን የተሳሳተ አመለካከት ያላቅቀናል። ከእኛ መወገድ የሚገባቸው የተለያዩ ዓይነት እምነትና አስተሳሰቦች ይኖራሉ፣ ለምሳሌ ያህል አንድ ሕፃን እንዲሞት እግዚአብሔር የሚፈቅደው ከሚገባ በላይ እናቱ ስለምትወደው ነው የሚለውን መጥቀስ ይቻላል። ይህ ግን የሰይጣን ውሸት ነው፣ የእግዚአብሔርን እውነተኛ ማንነትና ባሕርይም የሚጻረር ነው። ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነን ስንገኝ እግዚአብሔር በማንኛውም መከራ ውስጥ ያሳልፈናል፣ የደረሰብን መከራም ይበልጥ እርሱን እንድናውቅ ያደርገናል።

አብርሃም በእግዚአብሔር ላይ ስላለው እምነት የምንማረው ትልቁ ነገር ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ነው። መታዘዙ ሊያስከትል የሚችለውን ማንኛውንም ነገር ግምት ውስጥ ሳያስገባ ለእግዚአብሔር መታዘዝን መርጦአል። ለእግዚአብሔር ታማኝ ስንሆን አይታለፍም ባልነው በማንኛውም መሰናክል ውስጥ ያሳልፈንና እርሱን ማወቅ ወደምንችልበት ደረጃ ያደርሰናል። ይሁን እንጂ እዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስ ቀድሞ የነበረንን የተሳሳተ እምነትና አመለካከት እርግፍ አድርገን ለመተው ፈቃደኛ መሆን ይኖርብናል። እንዲፈትነህ እግዚአብሔርን አትጠይቀው። ጴጥሮስ፡- «ወደ ወኅኒም ወደ ሞትም ከአንተ ጋር ለመሄድ የተዘጋጀሁ ነኝ» በማለት በልበ ሙሉነት ለኢየሱስ ተናግሮ ነበር፣ በእግዚአብሔር ፊት እንዲህ ያለ ድፍረትና ልበ ሙሉነት ሊኖርህ አይገባም (ሉቃ. 23፣33)። አብርሃም በፍጹም እንዲህ በማለት አልተናገረም፣ ግን እግዚአብሔርን በታማኝነት ተከተለ፣ እግዚአብሔር እምነቱን አነጻለት።

የምትፈልገው ምንድንነው?

«ስራስህ ታላቅ ነገርን ትፈጋጋለህን?» (ኢዮ. 45፣5)

ታላቅ ሰው ከመሆን ይልቅ ለራስህ ታላቅ ነገርን ትመኛለህን? የእርሱን ስጦታዎች ከመቀበል ይልቅ ከእርሱ ጋር በጣም የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖርህ ማለትም እርሱን እንድታውቅ እግዚአብሔር ይፈልጋል። የዚህ ዓለም ታላላቅ ነገሮች በአጋጣሚ የሚገኙና ጊዜያዊ ናቸው፡ ይመጣሉ ይሄዳሉ። እግዚአብሔር ግን ምንም ነገር በአጋጣሚ አይሰጠንም። በይበልጥ የምትፈልገው ስጦታዎቹን ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔርን እስከሆነ ድረስ ከእርሱ ጋር ግንኙነት የማድረግን ያህል ቀላል ነገር የለም።

ከእግዚአብሔር የምትፈልገው የተለያዩ ነገሮችን እንዲሰጥህ ከሆነ ራስህን ሙሉ በሙሉ ለእርሱ መስጠት ምን ማለት እንደሆነ በሚገባ መረዳት አትችልም። ምናልባትም በራስህ አመለካከትና መንገድ ክርስቲያን ሆነሃል። ስለዚህም «እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን እንዲሰጠኝ ለመንሁ፡ እርሱ ግን የጠበቅሁትን አረፍትና ሰላም አልሰጠኝም» በማለት ቅር ታህን የምታሰማ ሰው ልትሆን ትችላለህ። እግዚአብሔር ደግሞ የተለያዩ ነገሮችን እንዲሰጥህ ከእርሱ መለመንህን አንጂ እርሱን ራሱን እንዳልፈለግህ በተለያየ መንገድና ሁኔታ ያመለክትሃል። ኢየሱስ «ለምኑ ይሰጣችሁማል» ብሎአል (ማቴ. 7፣7)። የምትፈልገውን ነገር ከእግዚአብሔር መለመን ትችላለህ፡ እንዲህ ስለተባለ ግን ይህን ያህል አስፈላጊ ያልሆነ ነገር ከእርሱ መለመን የለብህም፡ ምክንያቱም ይበልጥ ወደ እርሱ በቀረብህ መጠን በዚያው ልክ ስለነገሮች መለመንህን ታቋርጣለህ። «አባታችሁ ሳትለምኑት የሚያስፈልጋችሁን ይሰጣችኋል» ይላል ቃሉ (ማቴ. 6፣8)። ታዲያ ለምን እንለምናለን ወይም እንጠይቃለን? የምንለምነው ይበልጥ እርሱን ወደ ማወቅ ደረጃ እንዲያደርሰን ነው።

ለራስህ ታላቅ ነገርን እየፈለግህ ይሆን? «ጌታ ሆይ፣ በመንፈስህ መሞላት እፈልጋለሁ» በማለት ጸልየህ ምንም መልስ አጥተሃል? ለዚህ ምክንያቱ ሙሉ በሙሉ ሕይወትህን ለእርሱ አለመስጠትህ ወይም ከአንተ በኩል የጐደለ ነገር ስላለ ሊሆን ይችላል። ከእግዚአብሔር ምን እንደምትፈልግና ለምን እንደምትፈልግ ራስህን መጠየቅ ትችላለህን? ወደፊት ከምትደርስበት ፍጹምነት አንጻር አሁን ላለህበት የፍጹምነት ደረጃ እግዚአብሔር ይህን ያህል ግምት አይሰጠውም። እግዚአብሔርን ይበልጥ የሚያሳስበው የአሁኑ ባርኮትህ ወይም ደስታህ አይደለም፡ ስለዚህም ወደ በለጠ ፍጹምነትና ሙላት ያደርስህ ዘንድ ያለሚቋረጥ በሕይወትህ ይሠራል። «እኛም አንድ እንደሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ» (ዮሐ. 17፣22)።

የምታገኘው ነገር

«በምትሂዱበት ስፍራ ሁሉ ነፍስህን ምርኮ ስድርጌ ስሰጥሃለሁ» (ኤር. 45፣5)

በእርሱ ለሚታመኑበት እግዚአብሔር የሚሰጠው የማይናወጥ ተስፋ ይህን ይመስላል «ነፍስህን እሰጥሃለሁ»፣ ሰው ከሕይወቱ የበለጠ ሌላ ምን ይፈልጋል? ሕይወት አስፈላጊና ወሳኝ ነገር ነው። «ነፍስህን ምርኮ አድርጌ እሰጥሃለሁ» ማለት በምትሄድበት ቦታ ሁሉ ሌላው ቀርቶ ገሃነም ብትገባ እንኳ ምንም ጉዳት አይደርስብህም ማለት ነው። ብዙ ጊዜ ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን በረከት ሌሎች እንዲመለከቱልን እንፈልጋለን። ይሁን እንጂ በኩራት ለሌሎች የምናሳያቸው እነዚያ ውድ የሆኑብን ነገሮች ሁሉ አንድ ቀን ይጠፋሉ። የማይጠፋውና ለዘላለም የሚኖር ዋናው ነገር በክርስቶስ ውስጥ የተሰወረ ሕይወታችን ነው (ቈላ. 3፣3)።

በሕይወትህ ውስጥ ትልቅ ለምትለው ነገር ምንም ደንታ እስከማይኖርህ ድረስ ከእርሱ ጋር የተሟላ ኅብረትና አንድነት ወደምታደርግበት ደረጃ እግዚአብሔር እንዲያደርስህ ተዘጋጅተሃል? ሕይወትህን ጨምሮ ሁሉን ነገር ለእርሱ ለመስጠትና ለማስገዛት ዝግጁ ነህ? አንድ ሰው ሙሉ በሙሉ ሕይወቱን መስጠቱ የሚታወቀው «ጌታ ሆይ፣ ይህስ?» ማለቱን ሲያቆም ነው። ከራስህ አመለካከትና ግምት ተጠንቀቅ። «ጌታ ሆይ፣ ይህስ?» በምትለው ነገር ሙሉ በሙሉ ሕይወትህን አልሰጠህም ወይም የሚገባህን ያህል በእግዚአብሔር አልታመንህም ማለት ነው። ሕይወትህን ከሰጠህ ግን እግዚአብሔር ምን ሊያደርግ እንደሚፈልግ ይህን ያህል የሚያሳስብህ ጉዳይ አይሆንም። ሁሉን ነገር ለእግዚአብሔር መተው ማለት የማያስፈልጉ ጥያቄዎችን መጠየቅን ማቆም ማለት ነው። ራሳችንን ለእርሱ ስንሰጥና ነገራችንን ለእርሱ ስንተው እግዚአብሔር «ነፍስህን ምርኮ አድርጌ እሰጥሃለሁ» ይለናል። ብዙ ጊዜ ሰዎች በሕይወት መኖርን የሚሰለቹት የሚኖሩት ሕይወት ከእግዚአብሔር እንደ «ምርኮ» የተቀበሉት ስላልሆነ ነው። ከዚህ የመሳቀቂያው መንገድ ሙሉ በሙሉ ሕይወትን ለእግዚአብሔር መስጠትና መተው ብቻ ነው። ራስህን ሙሉ በሙሉ መስጠት ደረጃ ላይ ስትደርስ በጣም ደስተኛ ከመሆንህ ሌላ በሚገኘው ውጤትም በጣም ትገረማለህ። ሕይወትህን ስትሰጠው ያለምንም መከልከልና ገደብ እግዚአብሔር ይረከብሃል። እዚያ ደረጃ ላይ ካልደረስህ ግን ያልታዘዝህበት ነገር አለ ወይም ቀለል ያለ ሕይወትን መኖር አልፈለግህም ማለት ነው።

ስለምንም ነገር እርግጠኛ አለመሆን

«... ወደፊት ምን እንደምንሆን ገና ለይተገለጠም» (1ዮሐ. 3፣2 ኢ.መ.ት)

ተፈጥሮአዊ ባሕርያችን ወደ ፊት ስለሚሆኑ ነገሮች እርግጠኛ መሆንን ይፈልጋል፤ ስለማንኛውም ነገር እርግጠኛ አለመሆንን እንደመጥፎ ዕጣ ፈንታ እንቈጥረዋለን። አስቀድሞ ወደ ታለመና ወደ ታቀደ ግብ መድረስን እንፈልጋለን፤ የመንፈሳዊ ሕይወት ባሕርይ ግን እንዲህ አይደለም። የመንፈሳዊ ሕይወት ባሕርይ በራሳችን እርግጠኛ አለመሆናችንን ማረጋገጥ ነው። ስለሆነም ባመቸን ቦታ ሁሉ ተደላድለን አንቀመጥም። ተፈጥሮአዊ ግንዛቤአችን «እንዲህ ያለ ቦታ ላይ ብሆንስ? እንዲህ ያለ ነገር ቢደርስብኝስ?» በማለት ይጠይቃል፤ በመሠረቱ ስላልነበርንበት ቦታ ወይም ስላልደረስንበት ነገር ግምት መስጠት አንችልም።

ስለማንኛውም ነገር እርግጠኛ መሆንን መፈለግ የሰው ተፈጥሮአዊ ባሕርይ ምልክት ነው፤ ስለምንም ነገር እርግጠኛ ሳንሆን በእምነት መጓዝ ግን የመንፈሳዊነት ምልክት ነው። በእግዚአብሔር እርግጠኛ መሆን ማለት ስለምንሄድበት መንገድ፣ ነገ ስለሚያመጣው ነገር እርግጠኛ አለመሆን ማለት ነው። ስለሚቀጥለው እርምጃችን እርግጠኞች አይደለንም፤ በአምላካችን በእግዚአብሔር ግን እርግጠኞች ነን። ራሳችንን ለእግዚአብሔር ስንተውና የሰጠንን ሥራ በታማኝነት ስንሠራ ሕይወታችን በአስደናቂ ነገሮች ይሞላል። የግል እምነታችንን ማስፋፋት ስንሞክርና ለግል እምነታችን ጥብቅና ስንቆም ውስጣዊ ሕይወታችን መሞት ይጀምራል። ይህ ደግሞ ስለእርሱ ባለን የግል እምነት ማመን እንጂ ራሱን እግዚአብሔርን ማመን ማለት አይደለም። ኢየሱስ «ካልተመለሳችሁ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ» አለ (ማቴ. 18፣3)። መንፈሳዊ ሕይወት እንድ ሕፃን ሕይወት ያለ ነው። ቀጥሎ ስለምናደርገው ነገር እርግጠኞች ባንሆንም እንኳ በእግዚአብሔር ማንነት ግን እርግጠኞች እንሆናለን። እርግጠኝነታችን የተመሠረተው በራሳችን እምነት ላይ ከሆነ ትምክህተኞች እንሆናለን፤ ነቃፊዎች እንሆናለን፣ ባለን እምነትና አመለካከት እንወሰናለን። ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ኅብረትና ግንኙነት ካለን ሕይወታችን የወደፊቱን ነገር በመናፈቅና በመጠበቅ በሚገኝ ደስታ የተሞላ ይሆናል። ምን እንደሆነ ባናውቅም እንኳ ወደፊት የሚሆነው ነገር ያጓጓናል። ኢየሱስ «በእኔ አምኑ» አለ እንጂ (ዮሐ. 14፣1) «ስለእኔ በሰማችሁት ቃል፤ ወይም ስለእኔ በያዛችሁት አመለካከት እርግጠኞች ሁኑ» አላለም። እርሱ በእንዴት ዓይነት መንገድ እንደሚመጣ እርግጠኞች ባንሆንም፤ እንደሚመጣ ግን እርግጠኞች እንሁን፤ እርግጠኞች የሆንንበትንም ሆነ ያልሆንንበትን ነገር በሙሉ ለእርሱ እንተውለት፤ ከዚያ በኋላ በታማኝነት እንጽና።

ምንም ሳንጨነቅበት የሚገለጽ ፍቅር

«ፍቅር ደታገሣል ቸርነትንም ያደርጋል ..» (1ቆሮ.13፣4)

ፍቅር በራሱ መንገድና ሁኔታ ፈንቅሎ ይወጣል እንጂ ብዙ የምንጨነቅበትና የምንጠበብበት ጉዳይ አይደለም። ጳውሎስ ስለፍቅር ገለጻ የሰጠው እንደ ሂሳብ ስሌት ሁሉ ስለነገሮች እርግጠኝነት አልነበረም። «ከእንግዲህ ወዲህ ምንም ክፉ ነገር አላስብም፤ ከእንግዲህ ወዲህ ሊየሱስ እንዳምን የሚፈልገውን በሙሉ አምናለሁ» በማለት ሐሳባችንና ሥራችንን ሁሉ በእርግጠኝነት አስቀድመን መወሰን አንችልም። ፍቅር በስሌት የሚሆን አይደለም። ፍቅር ብዙ ሳናስብበት ከውስጣችን ፈንቅሎ የሚወጣ ነገር ነው። «ከዛሬ ጀምሮ ኢየሱስ ባስተማረው መሠረት እኖራለሁ» ማለት አንችልም፤ መንፈሱ በራሱ መንገድ በሕይወታችን ሲሠራ ግን እኛ ሳናውቀውና ሳንጨነቅበት እርሱ በሚፈልገው ሁኔታ ስንኖር ራሳችንን እናገኘዋለን። ወደ ኋላ ዘወር ብለን ሕይወታችንን ስንመለከት ብዙ ሳናስብበት በሕይወታችን ስለተገለጸው ፍቅር እንረዳለን፤ ይህም የእግዚአብሔር ፍቅር በሕይወታችን ሲሠራ እንደነበር ዓይነተኛ ማስረጃ ነው። የእግዚአብሔር ሕይወት በእኛ ሕይወት ውስጥ ሲሠራ እንደነበር የምንረዳው ካለፍንበት በኋላ ነው።

የፍቅር መገኛ ምንጩ እግዚአብሔር እንጂ እኛ አይደለንም። የእኛን ተፈጥሮ ተገን በማድረግ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ውስጥ ይሠራል ብለን ማሰብ በፍጹም የማይቻል ነው። የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ውስጥ ሊኖር የቻለው «በተሰጠን በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለፈሰሰ» ነው (ሮሜ 5፣5)።

ምን ያህል እንደምንወደው ለእግዚአብሔር ለማሳየት የምንሞክር ከሆነ በእውነት እርሱን እንደማንወደው አንድ ማስረጃ ነው። ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር የሚገለጸው እኛ ሳናስበውና ሳንጨነቅበት ነው፤ በውስጣችን ካለው የራሱ ባሕርይ የተነሣ እንዲሁ ይፈስሳል። ወደ ኋላ ዘወር ብለን ስንመለከት ለምን አንዳንድ ነገሮችን እንዳደረግን ምክንያት አናገኝለትም፤ ምክንያቱም ያንን ነገር ያደረግነው ከውስጣችን ፈንቅሎ በወጣው በእግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ ነው። በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የእግዚአብሔር ፍቅር ከውስጣችን ይመነጫል፤ በዚህም የእግዚአብሔር ሕይወት በሕይወታችን ይገለጻል።